# ** እስላማዊው ነገረ ምልጃ **

በ'ወንጌላዊ' ሳሂህ አብዱል

01/13/2018ዓ.ም

**መግቢያ፡-** ይህ ፅሁፍ 'እስላማዊው ነገረ-ድነት' በሚል ርዕስ በተከታታይ እየቀረበ የሚገኘው ትምህርት አንዱ ክፍል ነው። ከርዕሱም መረዳት እንደሚቻለው በዚህ ፅሁፍ የነቢዩ መሐመድ አማላጅነት ለጥያቄ ቀርቧል። በፅሁፉ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ጥያቄዎች የተመለሱ ሲሆን በዋናነት ግን ትምህርቱ እስላማዊ መሠረት አለው ወይ? ደግሞም የነቢዩ መሐመድ ምልጃ በእርግጥ ልብን ያሳርፋል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው ተመልሰዋል። ፅሁፉ ሶስት ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን። የመጀመሪያው ስለ አስተምህሮው የተወሰነ ማብራሪያ የቀረበበት ነው፣ ከእርሱ በመቀጠል ስለምን የምልጃ አስተምህሮ(የነቢዩ መሐመድ ምልጃ) ስሜት እንደማይሰጥ በርከት ያሉ ሙግቶች የቀረቡበት ክፍል ይገኛል። መጨረሻ ላይ ደግሞ የምልጃን አስተምህሮ በተመለከተ መመለስ ይኖርባቸዋል የምላቸው ጥያቄዎች ለብቻ ተሰንደው ቀርበዋል። <u>*ምንጭ አጠቃቀሜን በተመለከተ ግር ለሚለው*</u> ሰው(ለራሴ እንዲመቸኝ አድርግ ስለተጠቀምኩ) የምመክረው ቢኖር የተመላከተው ምንጭ የቱን መፅሀፍ እንደሚወክል ያብራሩሁበትን ሕዳግ እንዲመለከት ነው። በፅሁፉ የተጠቀሱትን አመተ-ምህረቶች በተመለከተ የተለየ ማብራሪያ እስካልተሰጠበት ድረስ ሁሉም የግሪጎሪያውያንን የዘመን አቆጣጠር ያመለክታሉ። አፅንኦቶችን በተመለከተ የተለየ ማብራሪያ ካልቀረበበት በቀር ሁሉ የእኔ ናቸው።

በዚህ አጋጣሚ ይህን ፅሁፍ ለሚያነቡ ሙስሊሞች የሚኖረኝ ምክር፡- በዚህ ፅሁፍ የተነሳው ሀሳብ በቀጥታ ከድነታችሁ ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ ቁብ ሰጥታችሁ እንድታነቡትና ምን ማለት እንደሆነ ከቀደመ አመለካከታችሁ ጋር እንድታገናዝቡት ነው። በእርግጥ የቀረቡት ማስረጃዎች ተዓማኒ ሆነው ባይገኙ ወይንም የተደረሰበት ድምዳሜ(ወይንም የቀረበው ሙግት) የማያሳምን ከሆነ እንድትቀበሉት አላበረታታም። ደግሞም ልትቀበሉም አይገባም። ነገር ግን መረጃዎቹ ታማኝ መሆናቸውን አረጋግጣችሁ ድምዳሜውም ርቱዕ/sound/ መሆኑ ላይ እርግጠኛ ከሆናችሁ እንግዲያውስ የተነሳው ሀሳብ የዘላለም ሕይወታችሁን በተመለከተ የሚወስን እንደመሆኑ ዛሬ ነገ ሳትሉ ትክክለኛውንና የሚያዋጣችሁን መንገድ እንድትይዙ አሳስባለሁ። -- በተረፈ ጥሩ የንባብ ጊዜ እንዲሆንላችሁ ተመኘሁ።

**Grant me by your Intercession, for which I hope**

**A beautifull page instead of my ugly sins”**

***--Ibn Khaldun(d.1332)***

---

እስልምና እንደ ሐይማኖት ሰዎች ወደ ድነት የሚደርሱበትን መንገዶች ሲቀይስ፤ እንደ አንድ አማራጭ ለድነት ይበጃል ብሎ የያዘው ምልጃን ነው። በመልካም ስራ ባይሳካልን፣ በሚጠበቅብንም ያህል እምነት ባይገኝብን ከጉድ የሚያወጣን፣ ከጭንቅ የሚገላግለን ታዳጊ ያስፈልገናል በማለት ምልጃን እንደ መፍትሄ አቅርቧል።

በሌሎች አስተምህሮዎችም እውነት እንደሆነው ሁሉ በዚህም ረገድ ሁሉም ሙስሊም ወጥ የሆነ አቋም እንዳልያዘ በቅድሚያ ልንገነዘበው ይገባል። እስልምና ከሚጓደድበት ከተውሂድ አስተምህሮ ጋር በቀጥታ ይጋጫል በሚል አስተምህሮውን ከሽርክ የሚመድቡ ሙስሊሞች አሉና።

በጥንት ዘመን ከሚታወቁ ሙስሊም ቡድኖች ‘አመክንዮአዊያን’ በሚል የሚታወቁት ሙታዘላዊያን ምልጃን አምርረው በመቃወም ይታወቃሉ። የነዚህ ቢድኖች ክርክር ምልጃ የአላህን ፍትሐዊነት ያዛባል ከሚል የሚመነጭ ነው(Annemarie pg. 96)።

ለተውሂድ ከሚሰጠው አፅንኦት የተነሳ ምልጃን አምርሮ የሚቃወመው ሌላኛው አንጃ ደግሞ ወሐቢዝም ነው። የምልጃ አስተምህሮ ‘የአላህን ሁሉን ቻይነት’ እና ‘በሁሉ ቦታ መገኘት’ ጥያቄ ውስጥ ስለሚጥለው የእስልምና ምሰሶ የሆነውን ተውሂድን በቀጥታ ይፃረፋል ይላል። ይሁንና ግን ይህ ሲባል ወሐቢዝም እስላማዊ መሠረት ያለውን/የቁርአኑ ቢያከራክር እንኳን ሐዲሳዊ መረጃዎች ምልጃን የሚያስተምሩ ናቸው/ የምልጃን አስተምህሮ ሙሉ በሙሉ አይቀበልም ማለት አይደለም። ከዚህ ይልቅ የዚህ ቡድን ተቃውሞ አላህን እንዲያማልዱን ፍቀድ ብለን በመጠየቅ ፈንታ አማልዱን ብለን ነቢያቱን/ፃድቃኑን/ ልንጠይቅ አይገባም። የሚልና ጥያቄያችን ደግሞ ምድራዊ ጉዳዮችን/worldly matters/ የተመለከተ መሆን የለበትም ከሚል የሚመነጭ ብቻ ነው(Asiya pg. 15)።

ለዚህም እንዳስረጅ፦ ምልጃን ከሚቃወሙ እስላማዊ አንጃዎች አንዱ የሆነው ወሐብያ፣ በብዙ የሚታመንባቸው ሸይሁል ተይሚያን እንጠቅሳለን።  እኚህ ሰው ምልጃ ከተውሂድ ጋር ያነካካናል በሚል ተቃውሟቸው የሚታወቁ ናቸው። ይሁን እንጂ ይህን ሲሉ በእስልምና ምልጃ አንዳችም መሠረት የለውም ብለው በማመን አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እንደውም በአላህ ፊት ከየትኛውም ነቢይ በላይ ተቀባይነት ባላቸው በነቢዩ መሐመድ ማመን የምልጃ የመጀመሪያው መስፈርት እንደሆነ ሁሉ

አስተምረዋል። ታዲያ የተቃወሙት ምኑን ነው? ቢባል። ተቃውሞአቸው አንድም *ምልጃ ለሊ-ሓማንያንም ጭምር ይሰራል* የሚለውን እና *ያለ አላህ ፈቃድ ከአላህ ዘንድ አማላጅ አለን'* የሚለውን አመለካከት ነበር('Expound..' pg.294)። ስለሆነም የምልጃ አስተምህሮ በእስልምና ከፍተኛ ተቀባይነት አለው ብንል አንሳሳትም ማለት ነው።

ይህን የሚደግፉ ቁርአናዊ እና ሐዲሳዊ ማስረጃዎችን እዚህ ጋር ማንሳት ይኖርብናል። የሚከተሉትን የቁርአን አያዎች እንመልከት፡-

ሱራ40:7 "እነዚያ ዐርሹን የሚሸከሙት እነዚያም በዙሪያው ያሉት በጌታቸው ምስጋና ያወድሳሉ፡፡ በእርሱም ያምናሉ፡፡ «ጌታችን ሆይ! ነገሩን ሁሉ በእዝነትና በዕውቀት ከበሃል፡፡ ስለዚህ ለእነዚያ ለተጸጸቱት መንገድህንም ለተከተሉት ምሕረት አድርግላቸው፡፡ <u>*የእሳትንም ቅጣት ጠብቃቸው፡፡» ኢያሉ ለእነዚያ ላመኑት ምሕረትን ይለምናሉ፡፡*</u>"(1)

በሱራ2:225 "በእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ራሱን ቻይ ነው፡፡ ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም፡፡ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡ <u>*ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው?*</u> (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)፡፡ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ፡፡ ጥበቃቸውም አያቅተውም፡፡ እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው፡፡"

በሱራ21:28 "በፊታቸው ያለውንና በኋላቸው ያለውንም ሁሉ ያውቃል፡፡ ለወደደውም ሰው እንጅ ለሌላው አያማልዱም፡፡ እነርሱም እርሱን ከመፍራታቸው የተነሳ ተጨናቂዎች ናቸው፡፡"

ሱራ42:5 "(ከአላህ ፍራቻ) ሰማያት ከበላያቸው ሊቀደዱ ይቀርባሉ፡፡ መላእክትም ጌታቸውን እያመሰገኑ ያወድሳሉ፡፡ <u>*በምድርም ላለው ፍጡር ምሕረትን ይለምናሉ*</u>፡፡ ንቁ! አላህ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነው፡፡"

ከእነዚህ ከተጠቀሱት አያዎች በተጨማሪ ቁርአን በብዙ ቦታዎች(በተጨማሪ ሱራ10:339; 19:87; 20:109; 34:23; 42:5; 53:26 ይመ) ሐጢያተኛ ሙስሊሞች አላህ ፊት ምህረት የሚያገኙበትና የሚድኑበት ዕድል መኖሩን ይጠቁማል።

ለምሳሌም ከላይ በጠቀስነው የሱራ42:5 ንባብ መላዕክቶች በምድር ለሚኖሩ አማኞች ምህረት እንደሚለምኑ ተገልጿል። እንዲሁም በሱራ40:7 አሁንም መላዕክቶች *'...ከእሳት ይጠብቃቸው ዘንድ'* ለአማኞች(ለሙስሊሞች) እንደሚማልዱ ተመላክቷል። - የምልጃ መኖር እሙን ነው ማለት ነው!

ታዲያ መላዕክቶች ብቻ ናቸው ወይ የሚያማልዱት? በእርግጥ አይደለም። ከዚህ ይልቅ '....ለእርሱ አልረሕማን የፈቀደለት፣ ለእርሱም ቃልን የወደደለት ሰው...'(ሱራ20:109) ጭምር የምልጃ ስልጣን አለው።

---

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከድምዳሜያችን ጋር የማይስማሙ ሰዎች ከዚህ በታች የሚገኙትን የቁርአን ምንባባት 'ምልጃ በቁርአን ውጉዝ ነው!' ለሚለው ሙግታቸው ይጠቅሳሉ፡-

ሱራ6:94 "መጀመሪያም ጊዜ እንደ ፈጠርናችሁ ኾናችሁ የሰጠናችሁን ሁሉ በጀርባዎቻችሁ ኋላ የተዋችሁ ስትኾኑ የሰጠናችሁን ሁሉ በጀርባዎቻችሁ ኋላ የተዋችሁ ስትኾኑ ለየብቻችሁ ኾናችሁ በእርግጥ መጣችሁን= እነዚያንም እነሱ በእናንተ ውስጥ (ለአላህ) ተጋሪዎች ናቸው የምትሉዋቸውን አማላጆቻችሁን ከእናንተ ጋር አናይም፡፡ ግንኙነታችሁ በእርግጥ ተቋረጠ፡፡ ከእናንተም ያ (ያማልደናል) የምትሉት ጠፋ (ይባላሉ)፡፡"

---

(1) ሱራ በተመለከተ ፀላዮቹ መላዕክቶች መሆናቸውን የሚገልፁት ኢብን ቀይም ቀጥለው የሚሉት ይህን ነው "....ምሕረት ይደረግ ዘንድ መላዕክት ንስሀ ለሚገቡ አማኞች የሚያቀርቡት ምልጃ በእርግጥ ምሕረት የሚያስገኝ ነው Driving Pg.92

ሱራ7:53 “(የዛቻውን) ፍጻሜውን እንጂ ሌላ አይጠባበቁም፡፡ ፍጻሜው በሚመጣበት ቀን እነዚያ ከመምጣቱ በፊት የረሱት ሰዎች «የጌታችን መልክተኞች በእርግጥ በውነት መጥተዋል፡፡ ለእኛ ያማልዱም ዘንድ አማላጆች አሉሉን= ወይስ ከዚያ እንሠራው ከነበርነው ሌላን ሥራ እንሠራ ዘንድ (ወደ ምድረ ዓለም) እንመለሳለን=» ይላሉ፡፡ ነፍሶቻቸውን በእርግጥ አከሰሩ፡፡ ይቀጥፉት የነበሩትም ከእነርሱ ጠፋቸው፡፡”

እነዚህ ምንባባት ምልጃ አለን የሚሉ ሰዎች ነፍስ ለሰራችው ስራ ብቻዋን በምትፋጠጥበት የፍርድ ቀን በከስረት ውስጥ መሆናቸውን፣ አማላጅ አድርገው የያዟቸውም አካላት ሊረዷቸው እንደማይችሉ የሚያስረዱ እንደመሆናቸው በእርግጥ ምልጃን እንደሚቃወሙ አድርገን ብንወስድ ላንሳሳት እንችላለን። ይሁንና ያነበብናቸውን አያዎች በተመለከተ(2) ሊሰመርበት የተገባ ነጥብ አለ።

ይኸውም በተጠቀሱት ምንባባት ማናቸውም የምልጃ አይነት ሳይሆን የተወገዘው ያለ አላህ ፈቃድ ዕውቅና የተቸራቸውን ነው። አላህ ከፈለገ አማላጅ ሾሞ/መርጦ/ ምልጃቸውን የሚቀበልበትን መንገድ ግን ቁርአን አልዘጋም ብለን እናምናለን።

---

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ምልጃን በተመለከተ ቁርአን የፈለገውን አቋም እንኳን ቢያራምድ ሙስሊሞች ምልጃን በተመለከተ አለማመን የማይችሉ መሆኑን መቀበል ይኖርብናል።

የዚህም ምክንያቱ ሁለት ሲሆን። አንደኛው፦ ተዓማኒ የሆኑ ሐዲሶች ምልጃን በተመለከተ ግልፅና የማያሻማ መመሪያን በመያዛቸው ነው(በዚህ ፅሁፍ በብዛት ተጠቅሰዋል)። ስለዚህም ‘ቁርአን ምልጃን አያፀድቅም’ የሚል ድምዳሜ ላይ እንኳን ብንደርስ፤ ምልጃን በተመለከተ ሐዲሳት ግልፅ አስተምህሮ እስከያዙ ድረስ ሙስሊሞች ምልጃን ሊቀበሉ የሚችሉበት መንገድ ሙሉ በሙሉ እንዳልተዘጋ ማመን ይኖርብናል(ሙስሊሞች ቁርአን የመጀመሪያው ባለስልጣን ነው ይበሉ እንጂ። በተግባር ቀን በቀን የሚኖሩት በሐዲሳት መመሪያ ስለሆነ)።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ፦ በሚገርም መልኩ ‘ምልጃ ፍቁድ አይደለም’ የሚሉ ሙስሊሞች ጭምር ለሙታን በሚደረጉ የስርየት ስነስርአቶች የሚያምኑ መሆኑ ነው። ይህም ማለት በእስልምና ለሞቱ ወዳጆቻችን ይጠቅማል በማለት በሚፈፀሙ እንደ ፍትሐት ፀሎት፣ ዕዳ ክፍያ፣ የካሳ ሶላት፣ የካሳ ዘካ ወዘተ የሚያምኑ መሆኑ ናቸው(ሳሂህ አብዱል ገፅ.16)

ይህን ማለት ያስፈለገበት የራሱ ምክንያት አለን። ይኸውም አንዳንድ የእስልምና አንጃዎች(ቡድኖች ወይም Sects) ‘ምልጃን አንቀበልም!’ በማለት አስተምህሮው ከሚያስከትልባቸው መዘዝ ማምለጥ ስለማይኖርባቸው ነው።

ስለዚህ ‘አስተምህሮውን አልቀበልም!’ በማለት በቀላሉ ለማምለጥ የሚሞክሩትን ወገኖች ስናገኛቸው የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልንጠይቃቸው ይገባል። ለመሆኑ የማትቀበሉት ምልጃ የትኛውን ነው? በአላህ ፈቃድ ምልጃ እንደሚኖር የሚናገሩትን የቁርአን ምንባባትስ እንዴት ትረዷቸዋላችሁ? በፍትሀት ፀሎትስ ታምናላችሁ? ካመናችሁ በምልጃና በፍትሀት ፀሎት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ምልጃን የሚያስተምሩ የሆኑትን ሳሂህ ሐዲሶችንስ አትቀበሏቸውም ወይ? ደግሞስ የአሕለል ሱናው አቋም ምልጃ እንዳለ የሚገልፅ በሆነበት ከዚህ አቋም የተለየን አመለካከት መያዝ ትችላላችሁ ወይ(የአሕለል ሱናው አቋም ከዚህ በታች የቀረበው ነው)?

እዚህ ጋር ካደረሳችሃቸው በእርግጠኝነት የተነሱትን ጥያቄዎች ስለማይመልሱ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ቁርአን በሚጠቁመው የምልጃ አይነት እናምናለን የሚል ይሆናል። ይህን ጊዜ ቀጣዩን ውይይት ትጀምራላችሁ ማለት ነው።

---

(2) በፍርድ ቀን የአማላጆች ምልጃ ለማንም እንደማይጠቅም የሚናገሩ ተጨማሪ ምንባባትን፣ እንዲሁም በፍርድ ቀን ራሱ አላህ ብቻ እንደሚያማልድ/ወደማን እንደሚያማልድ ባይታወቅም/ የሚጠቁሙ ተጨማሪ አያዎች ካስፈለጉ ሱራ30:13; 36:23; 39:43; 40:18; 74:48። ሱራ6:51; 6:70; 10:18; 32:4; 39:44 ይመ

ዋናው ኢስላም የሚወክለው የምሁራን ስብስብ(አሕለል-ሱናው)፣ ምልጃን በተመለከተ ያለው አቋም አዎንታዊ ነው። ምልጃ ቁርአናዊም ሐዲሳዊም መሠረት አለው ብሎ ያምናል።

ጉምቱው ምሁር ኢማሙ አልገዛሊ በአንቀፀ ሐይማኖታቸው አማኝ ነኝ የሚል ሙስሊም ሊያምናቸው ይገባል በሚል ከዘረዘሯቸው ነጥቦች አንደኛው እንዲህ ይነበባል፦ “(አማኝ) ነኝ የሚል ሰው በነቢያቶች፣ በኡለሞች፣ በሰማዕታት፣ እንዳሁም በአማኞች ምልጃ ማመን ይኖርበታል።…”-(3)

ሙስሊም ምሁር ኢብን አል-ቀይም(d.1292) አሕለል-ሱናው ምልጃን በተመለከተ የያዙትን አቋም ያጠቃለሉት የሚከተለውን ብለው ነው፦

“አሕለል ሱናው በነቢዩ መሐመድ አማላጅነት በእርግጥ ያምናል። ይኸውም ከዑመቱ ከባድ ሐጢያት ለፈፀሙ የሚሆን ነው” –(Driving pg. 22)።

ስለሆነም እስልምና ሐጢያተኛን ሊመነዳ ብሎም ሐጢያት አጥቦ ጀነት ሊያስገባ በሚችል ምልጃ ያምናል ማለት ነው።

አስተምህሮው አንድን ሰው ከመልካም ስራውና ከእምነቱ በተጨማሪ ጀነት ለመግባት መተማመኛን የሚሰጠው ነው። ድንገት ድጦህ ብትገኝ ፍፃሜህ ዘላለማዊ ጥፋት እንዳይሆን እነ እከሌ አሉልህ ይለዋል። -- ‘የአደጋ ጊዜ መውጫ’ን ሲጠቁመው

ከማመን ውጪ አማራጭ የሌለው ተስፈኛም፣ ‘አላህ እንኳን ቢጨክንበት’ የሚታደገውን አዳኝ ያገኘ ስለሚመስለው በልበሙሉነት ይጓደዳል።

ከዚህ በታች የቀረበው የጉምቱው ሙነሺድ የሙሐመድ አወል ስንኝ ይህን የሙስሊሞች መተማመን የሚያንፀባርቅ ነው።

ተጀሐነም ጀርባ ሲራጥ ሲተከል

ስራችን ሲመዘን ቢሞላም ቢጎድል

መሐመድ ይቆማል፣ ለመገላገል

⋮

⋮

ታላላቁን ሁላ ያ ቀን ሲያዋርደው

መሬቱን ሰማዩን ጀሊል ሲናንደው

ሰባቱን ምድኝ አዝዞ ሲያስነድደው

ሰውና ድንጋይ ነው እዚያ የሚማገደው

ሙሐመድ ብቻ ነው ከአልጋው የማይወርደው

የጀሊሉን ቁጣ ለምኖ የሚያበርደው(4)

---

(3) Watt pg. 78 በተጨማሪም ገፅ 54 ይመ። ዋናውን እስላም የሚወክሉ ከሆኑት የሱኒ መዝሀቦች ቢያንስ ሶስቱ ሐንበሊያ፣ አሻሪያ እና ሐነፋይት ምልጃን በተመለከተ ለጥርጣሬ ክፍተት በማይሰጥ መልኩ እንደሚያምኑበት ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገ Watt pg. 31, 44, 60 ይመ)

(4) ‘ጀማሉ’ ከተሰኘው የሙሐመድ አወል መንዙማ የተወሰደ ስንኝ https://youtu.be/0GyD9CPcdxE?si=YpfisJlmCPGvm0lJ

ታዲያ ከላይ እንደገለፅነው ምንም እንኳን ትምህርቱን የማይቀበሉ ጥቂት ሙስሊሞች ቢኖሩም በቁርአንና በሐዲስ በተግባራዊ ምሳሌዎች ተደግፎ የቀረበ ትምህርት እንደመሆኑ ዋናው እስላም ያለ ጥርጥር ሊቀበለው ችሏል። በዚህም ፅሁፍ የተንፀባረቀው ይኸው ሀሳብ ነው። - እንቀጥል።

---

የሰው ልጆች ሁሉ ከሞት ተቀስቅሰው በአንድ ቦታ ከሚከማቹበት ከዚያ ቀን አንስቶ የምልጃው ስነ-ስርአት እስከሚከናወን ባለው ጊዜ ምን እንደሚካሄድ በወፍ በረር በማየት እንጀምር፡-

በዚህም ሰማይና ምድር እንዲጠፉ ከተደረገ በኋላ ከመቃብር በታች ያሉ ሙታኖች/ፃድቁም ሓጥዑም/ ተቀስቅሰው በአንድ ገላጣ ሜዳ እንዲሰበሰቡ ይደረጋል። በቀኑ(5) የሰው ዘር በሙሉ ለመመርመርና በውጤቱም የሚገባውን ፍርድ ለመቀበል በተዘጋጀ መልኩ ራቁቱን(ወንዱም ሴቱም) ሁሉን በሚችለው አላህ ፊት ተሰድረው እንዲቆሙ የሚደረግ ሲሆን። ይህም በዘይቤያዊ ትርጉሙ ከተረዳነው ምንም ነገር ከማይሰወርበት ሁሉን አዋቂው ጌታ ፊት በግላጭ መሰጣትን ያመልከታል።

በዚህ መድረክ ከሚሆኑ ሁነቶች አንደኛው የስራ መዝገብ ተገልጦ ሰዎች በምድር ቆይታቸው ለሰሩት መልካምም ይሁን ክፉ ስራ የሚጠየቁበት ወይንም የሚከላከሉበት /Justification/ ይሆናል። ከእያንዳንዱ ሰው ግራና ቀኝ ትከሻ ላይ ሁነው መልካምና ክፉ ስራችንን ሲመዘግቡ የነበሩ ሙንከርና ነኪር ሪፖርታቸውን የሚያቀርቡበት አስፈሪ ዕለት።

ስለሆነም በነጭና በጥቁር የተመሰሉት ደብተሮቻቸው ሊመሰክሩልን አልያም ሊመሰክሩብን በአየር ላይ እየበረሩ በእያንዳንዱ ላይ እንዲሰፍሩ ይደረጋል(6)። ያ ቀን አላህ ፍርድ ለመስጠት በቆየበት መጠን አስጨናቂነቱ የዚያኑ ያህል ይጨምራል። የዚህም ምክንያቱ በዕለቱ ራቁታቸውን የተሰለፉት ነፍሳት አናት ላይ ፀሐይ እንድትቀርብ ስለምትደረግ ነው።

ሙስሊም ፀሐፊያን ፀሐይቱ በተሰብሳቢዎቹ አናት ላይ የምትቀርብበትን ርቀት በተመለከተ የተለያየን ቁጥር የሚያስቀምጡ ሲሆን። ብዙዎቹም በዕለቱ ፀሐይ የስንዝር ያህል ርቀት ብቻ እንደሚኖራት ሲገልፁ። የቲርሚዲህ 2606 ዘገባ መሠረት ያደረጉ ፀሐፊያን ደግሞ አንድ ማይል(1.6ኪሜ) ርቀት ብቻ እንዲኖራት እንደሚደረግ ይገልፃሉ(Bah pg. 28)

የፀሐይቱ ወደ ተሰብሳቢዎቹ በዚህ መጠን የመጠጋት  አላማ ተሰብሳቢዎቹን እንደየስራቸው መጠን በግለቷ እንድታንፈቀፍቃቸው ነው(ልብ አድርጉ ይህ ቅጣት እንግዲህ ገና ፍርድ ሳይሰጥ በፊት የሚሆን ነው።) በዕለቱ ፀሐይቱ ከምትለቀው ከፍተኛ ሙቀት የተነሳ አንዳንዱን እስከ ወገቡ ድረስ በላብ ስትዘፍቀው፣ ሌሎችን ደግሞ እስከ ወገባቸው ድረስ በላብ ታጥለቀልቃቸዋለች። በጣም መጥፎ ስራ የሰሩትን ደግሞ እስከ አፍንጫቸው ድረስ በላብ እንዲጠመቁም ታደርጋለች። (ቡሐሪ ቅፅ2 መፅ24 ቁ.553 በተጨማሪም Hajar pg. 34 ይመ)

ዕለቱ ዕጣፈንታችንንና ዘላለማዊ መኖሪያችን የሚወሰንበት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ ፍርድ እስከሚተላለፍ ድረስ ባለው ጊዜ መከራ የሚዘንብበት ቀን ከመሆኑ የተነሳ እጅግ አስጨናቂ እንደሆነ ይታመናል።

---

(5) ይህ ቀን በተለያዩ ሙስሊም ፀሐፊዎች የተለያየ ስያሜ ሲኖረው። የተወሰኑትም 'የትንሳኤ ቀን'፣ ሰዓቲቱ"፣ 'የሒሳብ ቀን'፣ 'የፍርዱ ቀን'፣ 'የውመል ቂያማ'፣ 'የመጨረሻው ቀን'፣....ወዘተ ተብሎ ይጠራል

(6) እዚህ ጋር የሚከተለውን ጥያቄ ማንሳት እንችላለን። ይኸውም ይህ ቀን/የውመል ቂያማ/ ከመምጣቱ በፊት ነፍሳት በምድር ቆይታቸው የሰሩት መልካም ወይንም ክፉ ስራ መሠረት ተደርጎ ክፉ የሰሩ በመቃብር እንዲቀጡ  መልካም ያደረጉ ደግሞ በጀነት እንዲቀማጠሉ ከተደረገ በኻላ ከሆነ የሚመጣው እንደገና በዚህ ቦታ ስራቸውን መመርመሩ ወይንም መመዘኑ ለምን አስፈለገ? መጀመሪያውኑ ስራቸው ስለታወቀ አይደለም ወይ ከተለያየ ቦታ መጠራታቸው/ከመቃብር እና ከጀነት/?

የቀኑን አስጨናቂነት አንዳንድ ፀሐፊያን የገለፁት ሰዎቹ እጅግ ከመጨነቃቸው የተነሳ *'ወደ ገሐነም እንኳን ቢሆን ለመግባት ይፈልጋሉ'* በሚል ነው። የሸህ ሰይድን ቃል ስንዋስ፡- "የሰው ልጆች ከትንሳኤ በኻላ በፍርድ ሸንጎ ሲቆሙ ይጨነቃሉ፣ ይሸበራሉ። ወደ ገሃነምም ቢሆን ለመሄድ ይመኛሉ። አማላጅም ይፈልጋሉ"-(ሚስዮናዊያን ገፅ. 281)። እንግዲህ ይህን ከመሰለው ገለፃ በመነሳት አንባቢያን የመከራውን ብርቱነት መረዳት ይቀላቸዋል ብለን እናስባለን።

ዕለቱን አስጨናቂ የሚያደርገው ሌላኛው ጉዳይ የቆይታ መጠኑ ነው። በዚህ መልኩ የሚሰቃዩ ወገኖች ስቃያቸው የሚቆየው ለደቂቃዎች፣ ለሰዓታት፣ ወይንም ለተወሰኑ ቀናት አይደለም። ለአመታት እንጂ

ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ ባለው የጊዜ መጠን ላይ ሙስሊም ፀሐፊያን አሁንም ልዩነት ማሳየታቸውን ልናነሳ እንወዳለን። ሱራ32:4ን በመጥቀስ ለአንድ ሺህ አመት ነው ከሚሉ አንስቶ ሱራ70:4ን በመጥቀስ ለ50,000 አመት ይቆያል እስከሚሉ ድረስ ልዩነቶች ታይተዋልና(ft. HADDAD pg.75፤ Geisler pg. 129።)

አንድ ሙስሊም ፀሐፊ ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ ቢያንስ 50,000 አመት እንደሚቆይ ይገልፁና። ይህ እስኪፈፀም ግን ሐጢያት የሰሩ ሰዎች እየተቀጡ እንደሚጠብቁ ያትታሉ። በምሳሌነትም ያነሱት ዘካን ስለማይከፍሉ ሰዎች ነው። እንደ እርሳቸው ከሆነ ዘካን ያልከፈሉት ሰዎች ፍርድ እስኪፈፀም ድረስ ባሉት 50,000 አመታት በጋለ መጥበሻ እየተገላበጡ እንዲጠበሱ ይደረጋል - በተጨማሪም ውሸት የዋሹ ሰዎች አፋቸው ውስጥ ጉጠት ገብቶ መንገጭላቸውን እየጓጠው እንደሚሰቃዩ፣ ቁርአን ያልቀሩ ሰዎች መሬት ላይ ተዘርረው በድንጋይ አናታቸው እንዲፈረከስ፣ ወለድ የበላ በደም ባህር ውስጥ እንዲቆይ ተደርጎ በድንጋይ እንደሚጨፈጨፍ፣ ዝሙተኞች ራቁታቸውን እሳት ውስጥ እንዲዘፈዘፉ፣....ወዘተ እንደሚደረግ ፅፈዋል (Bah pg. 29 እና 47 ይመ)

በሚያስገርም መልኩ ታዲያ ይህ የስቃይ ጊዜ ኢ-አማኙን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን አማኞችንም የሚያጠቃልል መሆኑ ነው። ለዚህ ማስረጃው በቡሐሪ ቅፅ9 መፅ93 ቁ.507 ነው። በዚህ ሐዲስ አማኞች/ሙስሊሞች/ ይሉታል የተባለው የሚከተለውን ነው፡- “አማኞችም ይላሉ: ‘ከዚህ አስፈሪ ቦታ የሚታደገንን ሰው ፈልገን እንዲያማልደን እንጠይቀው’። ከዚያም ወደ አዳም ይሄዳሉ...”

እንግዲህ ይህ ሁሉ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው፤ ሲቃዩ ሲጠናባቸውና ሰማዩ ሲደፋባቸው *'በውኑ ከዚህ መከራ ሊያድነን የሚችለው ማነው?'* ብለው በመመካከርና አማላጆች እንደሚያስፈልጓቸው በማመን አይናቸውን ወደ ነቢያቱ የሚያነሱት።

---

ምልጃ(7) ቁርአናዊ መሠረት እንዳለውና ከዚህም የተነሳ ዋናውን መስመር የሚከተሉ ሙስሊሞች እንደሚቀበሉት ካየን ዘንዳ፤ ቀጣዩ ጉዞአችን ለዚህ አስተምህሮ መሠረት ጥለዋል የሚባሉትን ሐዲሶች በቅርበት ወደ መመርመር ይሆናል።

---

7. የምልጃ አስተምህሮን ተቀባይነት እንዲያገኝ ያስቻሉ ታሪኮች በእስላማዊ ምንጮች መኖራቸው ሙስሊሞች አስተምህሮውን ሳይጠራጠሩ እንዲቀበሉ አስችሏቸዋል። ለምሳሌ በሚከተለው ሐዲስ የሚገኘውን ታሪክ እንመልከት፡- በሳሂህ አልቡሐሪ3342 መፅ60 ቁ.17 እና ሳሂህ አል-ቡሐሪ349 መፅ8 ቁ.1 ላይ ነቢዩ መሐመድ በሚራጅ ጉዞ ወቅት የተለያዩ ነቢያቶችን በሰማይ ላይ እንደተገናኙ ይገልፃል። አናስ ቢን ማሊክና ኢብን ሐዝም እንደተረኩት ከሆነ ነቢዩ መሐመድ ለዑመታቸው ያዝዙት ዘንድ 50 ሶላት በአንድ ቀን ተመድቦባቸው እየተመለሱ እያለ ሙሳ ያገኛቸውና እንዲህ ሲል ይጠይቃቸዋል ‘አላህ የሰጠዎት ትዕዛዝ ምንድን ነው?’ ሲመልሱ ‘አላህ ለዑመቶቼ 50 ሶላትን ደንግጓል’ አሉ። በዚህ ጊዜ ሙሳ ‘ ዑመቶት ይህን ሁሉ ሶላት መስገድ ስለማይችሉ፣ ተመልሰው በመሄድ ቀንስላቸው በሉት?’ ይላሉ። መሐመድም በመመለስ አላህ ከወሰነው ቁጥር ላይ እንዲቀንስ ሲጠይቁት። ግማሹን ይቀንስላቸዋል። ይህንን ይዘው እየሄዱ እያለ አሁንም ሙሳ ያገኛቸውና። ‘አሏህ ለዑመቶት ስንት ሶላት አዘዘ?’ አላቸው። ግማሹን ቀንሶልኛል(25 መሆኑ ነው) ሲሉት። ‘ዑመቶት ይህን ሁሉ መወጣት ስለማይችሉ አሁንም ተመልሰው በመሄድ ይቀንስላቸው ዘንድ ጠይቁት?’ አላቸው። ተመልሰው አላህን ሲጠይቁት ግማሹን(12/13 መሆኑ ነው) ይቀንስላቸዋል። ይህንንም ይዘው እየተመለሱ እያለ

በዚህም ለአስተምህሮው ድጋፍ በብዛት ከሚጠቀሱት ውስጥ አራቱን ብቻ እንመልከት፡- አንደኛው የሚገኘው በሳሂህ አል-ቡሐሪ4476 መፅ65, ቁ.3 ነው፡- “ከአነስ ተዘግቧል፤ ነቢዩ እንዲህ አሉ ‘በትንሳኤ ቀን ምእመናን ይሰበሰባሉ፤ ከዚያም ‘ወደ ጌታችን የሚማልድልን ሰው ብናገኝ! ይላሉ። ከዚያም ወደ አደም ይሄዳሉ፤ እንዲህም ይሉታል ‘አንተ የሰዎች አባት ነህ። አላህ በእጁ ፈጠረህ፣ መላእክቱንም ለአንተ እንዲሰግዱ አዘዘ፤ የነገሮችንም ሁሉ ስሞች አስተማረህ። ስለዚህ ከዚህ ቦታችን እንዲያሳርፈን ለእኛ በጌታህ ዘንድ ምልጃ አድርግልን።’ እርሱም ‘ለዚህ የሚገባኝ አይደለም’ ይላል፤ ከዚያም ኃጢአቱን ያስታውሳልና ያፍራል። ከዚያም ‘ወደ ኑህ ሂዱ፤ እርሱ አላህ ወደ የምድር ሰዎች የላከው የመጀመሪያው መልእክተኛ ነው’ ይላቸዋል። ወደ ኑህም ይሄዳሉ። እርሱም ‘ለዚህ የሚገባኝ አይደለም’ ይላል። ስለ እርሱ ዕውቀት የሌለውን ነገር ጌታውን የጠየቀበትን ጉዳይ ያስታውሳልና ያፍራል። ከዚያም ‘ወደ አር-ረሕማን ወዳጅ፣ ወደ ኢብራሂም ሂዱ’ ይላቸዋል። ወደ ኢብራሂምም ይሄዳሉ። እርሱም ‘ለዚህ የሚገባኝ አይደለም፤ ወደ ሙሳ ሂዱ፤ እርሱ አላህ ያነጋገረውና ተውራትን የሰጠው ባሪያ ነው’ ይላቸዋል። ወደ ሙሳም ይሄዳሉ። እርሱም ‘ለዚህ የሚገባኝ አይደለም’ ይላል፤ ነፍስን ያለ ሌላ ነፍስ [በቀል] የገደለበትን ጉዳይ ያስታውሳል፤ በጌታውም ፊት ያፍራል። ከዚያም ‘ወደ ዒሳ ሂዱ፤ እርሱ የአላህ ባሪያ፣ መልእክተኛው፣ የአላህ ቃልና ከእርሱ የሆነ ሩሕ ነው’ ይላቸዋል። ዒሳም ‘ለዚህ የሚገባኝ አይደለም፤ ወደ መሐመድ ሂዱ እርሱ አላህ ያለፈውንና የሚመጣውን ሁሉ ይቅር ያለለት ባሪያ ነው’ ይላቸዋል። ከዚያም ወደ እኔ ይመጣሉ። እኔም ወደ ጌታዬ ሄጄ ፈቃድ እጠይቃለሁ፤ ፈቃድም ይሰጠኛል። ጌታዬን ሳይ በሱጁድ እወድቃለሁ፤ አላህም እንደፈቀደው ያህል በዚያ ሁኔታ ይተወኛል። ከዚያም ‘ራስህን አንሳ፤ ጠይቅ ይሰጥሃል፤ ተናገር ይሰማሃል፤ ምልጃ አድርግ ምልጃህም ይቀበላል’ ይባልልኛል። ከዚያም ራሴን አነሳለሁ፤ እርሱ በሚያስተምረኝ የምስጋና ቃላት አላህን አመሰግነዋለሁ። ከዚያም ምልጃ አደርጋለሁ፤ እርሱም ለእኔ የተወሰነ ገደብ [የምማልድላቸውን ሰዎች] ይወስንልኛል፤ እኔም ወደ ጀነት አስገባቸዋለሁ። ከዚያም ወደ እርሱ እመለሳለሁ፤ ጌታዬን ሳይ እንደ ቀድሞው እሆናለሁ፤ ከዚያም ደግሜ ምልጃ አደርጋለሁ። እርሱም ሌላ የተወሰነ ገደብ ይወስንልኛል፤ እኔም እነርሱን ወደ ጀነት አስገባቸዋለሁ።’ ከዚያም ለሦስተኛ ጊዜ እመለሳለሁ፤ ከዚያም ለአራተኛ ጊዜ እመለሳለሁ፤ ከዚያም፡- ‘በእሳት ውስጥ የቀሩት ቁርኣን የከለከላቸው እና በእነርሱ ላይ ዘላለማዊ መቆየት የተወሰነባቸው ብቻ ናቸው’ እላለሁ።»

ይህ(8) ሐዲስ በተለምዶ የ’ምልጃ ሐዲስ/Haddith of Intercession/’ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን የነቢዩ መሐመድን አማላጅነት የተመለከቱ ትምህርቶች ላይ ሁሉ የማይጠፋ ታዋቂው ሐዲስ ነው። ሐዲሱ ከተመለከተው ምንባብ በተጨማሪ ከተወሰኑ የቃላት ልዩነቶች ጋር በተለያዩ ስፍራዎችም ይገኛል(9)

---

ሙሳ ያገኛቸዋል። ‘አሏህ ለዑመቶት ስንት ሶላት አዘዘ?’ ሲል በድጋሚ ይጠይቃቸዋል። ግማሹን ቀንሶልኛል ሲሉት። ‘ዑመቶት ይህን ሁሉ ስለማይችሉ አሁንም ተመልሰው በመሄድ ይቀንስላቸው ዘንድ ጠይቁት?’ አላቸው። ለአራተኛ ጊዜ በአላህ ፊት ቀርበው ሲጠይቁት ‘ከ50 ሶላቶች ጋር እኩል ዋጋ ያላቸውን 5ት ሶላቶች እሰጥሀለሁ። ውሳኔዬን ከእንግዲህ አልለውጥም’ አላቸው/ …for My Word does not change/.” ይህ ሐዲስ በሁለት መልኩ ለምልጃ አስተምህሮ በር ከፍቷል ማለት እንችላለን። አንደኛው፡- በምንባቡ እንደተመለከትነው ነቢዩ መሐመድ ከተርታው ሰው በዘለለ የነቢያቱን እንኳን ቅሬታ ፈቺ ሆነው ነው የቀረቡት። ስለሆነም ነቢዩ ሙሳ እንኳን አላህን የጠየቁት በመሐመድ በኩል ነው የሚል ትምህርት የሚገኝበትን ይህን የመሰለውን ሐዲስ አምኖ የሚቀበል ሙስሊም በቀጥታ አላህን መጠየቅ ድንበር መጣስ መስሎ እንዲሰማው ያስችለዋል ማለት ነው። ሌላው/ሁለተኛው/፡- በዚህ ሐዲስ ነቢዩ መሐመድ የአሏህን ድንጋጌ በልመናቸው መቀየር እንደሚችሉ ተመላክቷል። ይህም በዕለተ ቂያማ አላህ የሚያሳልፍብኝን ውሳኔ ተለማምነው ያስቀይሩልኛል ለሚለው አመለካከት መሠረት ጥሏል።

8). ይህ ሐዲስ በጠባዩ በመፅሀፈ ራዕይ የምናቀውን የማሕተሙን ታሪክ ለመሸፈን የቀረበ ይመስላል። ትረካው በሙሉ ልብ እንዳንቀበለው የሚያደርጉ ነጥቦች ያሉት ሲሆን የተፈበረከበትም ዓላማ ነቢዩ መሐመድ ነቢያቶች እንኳን መፍታት ያልቻሉትን እንቆቅልሽ የመፍታት አቅም እንዳላቸው አደርጎ ለመሳል ይመስላል።

የምልጃውን ትረካ  በያዙት ሐዲሶች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ቀጥለን እንመልከት፡-

#1. -ከቲርማዲህ 3148 መፅ47 ቁ.200 በቀር ትረካውን በያዙት ሌሎች ሐዲሶች ላይ ኢየሱስ የቀረበለትን የአማልደን ጥሪ ለመሐመድ ሲያስተላልፍ 'ሐጢያትን አለመጥቀሱ' ተዘግቧል። ሐሰን በሆነ የቲርሚዲህ ዘገባ ላይ ግን ለየት ባለ መልኩ ሰዎች '... *ከአላህ ውጪ አምልከውኛል*' በማለት ጥያቄውን እንዳልተቀበለ ተፅፏል። (10)

#2. ቡሐሪ ቅፅ9 መፅ93 ቁ.601 ላይ  ሶስት ነቢያቶች ናቸው የተጠቀሱት። ቅብብሎሹም አዳም→ ኑህ→ አብርሀም፣ ሙሳ→ ኢሳ→መሐመድ **ሳይሆን** አደም→ኑሕ→መሐመድ ነው። በሳሂህ ቡሐሪ ቅፅ2 መፅ24 ቁ.553 መሠረት ደግሞ ቅብብሎሹ አዳም→ ሙሳ→ መሐመድ ሆኖ ቀርቧል። በቡሐሪ7510 መፅ 97, ቁ. 135 ደግሞ አዳም በቀጥታ ወደ አብርሀም ነው የጠቆመው። ሳሂህ ሙስሊም193 መፅ1 ቁ. 385 እንዲሁም ቡሐሪ3340 መፅሀ 60 ቁ.15 ላይ *'...ወደ መሐመድ ብትሄዱ ይሻላል'* የሚለው ኢየሱስ **ሳይሆን** አብርሀም ሆኖ ቀርቧል።

#3. በቡሐሪ4712 መሠረት ሁሉም የሰው ዘር እንደሚሰበሰብ ይናገራል። '...Allah will *gather all the human being* of early generations as well as late generation on one plain...'(ይሁንና በቡሐሪ7410 መሠረት ደግሞ አላህ አማኞችን ብቻ እንደሚሰበስብ ይናገራል። *'...አላህ ምዕመናንን ይሰበስባል'*)።

#4. በቡሐሪ7440 መሠረት ኑሕ የመጀመሪያው ነቢይ ተብሏል። ነገር ግን በሌሎቹ ዘገባዎች የመጀመሪያው መልዕክተኛ ሆኖ ነው የቀረበው።(የመጀመሪያ ነቢይ አዳም እንደሆነ ግን የሚታወቅ ነው)።

ወደ ሐዲሱ ትምህርት ስናልፍ፡-  በቀረበው የምልጃ ትረካ አምስቱም ነቢያቶች።  የቀረበላቸውን የ'አማልዱን' ጥሪ ወግድ ያሉት በሌላ ሳይሆን *'ሐጢያት አለብን'* ብለው በማመናቸው ነው። ነቢያቱ በዚህ እምነታቸው እየነገሩን ያለው  *'እጅግ ቅዱስ በሆነው አምላክ ፊት እንኳን ለመማለድ ይቅርና ለመቆም እንኳን ከሐጢያት ንፁህ መሆንን ይጠይቃል'* የሚል ነው። ምልጃ 'ሐጢያት አልባነትን' በመስፈርትነት ይጠይቃል ማለታቸው ነው።

እንግዲህ እኛም በነቢዩ መሐመድ አማላጅነት የሚያምኑ ሙስሊም ወዳጆቻችንን በመጀመሪያ እንዲመልሱት የምንፈልገው ጥያቄ ነቢዩ መሐመድ በእርግጥ ይህን መስፈርት ያልፉታል ወይ? ብለን ነው።

---

9). የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው  Bukhari 3340, 4476, 4712, 7410, 7440, 7510 ሙስሊም193a, 193e, 194, 195 Tirmidhi2434, 3148 Ibn Majah4312, Mishkat5572

(10).  ሰይድ መሐመድ ሰዲቅ 'እስልምና እና ሚስዮናዊያን' በሚለው መፅሀፋቸው ለኢየሱስ የ'አማልደን' ጥሪ ሲቀርብለት የመለሰው ብለው ያሉት '...ወደ የሱዕ/ኢየሱስ/ ይሔዳሉ፣ እርሱም 'እኔና እናቴን ተገዙኝ ያልከው አንተ ነህን?' በማለት ተወቅሻለሁ ይላል። ሁሉም ነፍሴን ነፍሴን ሲሉ፣ ምስጉን ደረጃ የተሰጠው ታላቁ መሐመድ አምላኩ ፊት ለምልጃ በግንባሩ 4ጊዜ ይደፋል። ምልጃው ይሰማል።...' በማለት ነው(ገፅ. 282 ቅንፍ የእኔ)። እዚህ ጋር ሼሕ ሰይድ ሀሳቡን ያገኙበትን ምንጭ አለመጥቀሳቸውን ሳንረሳ። የጠቀሱት ታሪክ እውነት ነው ብለን ተቀብለን የሚከተለውን ጥያቄ እናንሳ፦ በዚህ ቦታ ኢየሱስ/ዒሳ/ 'እኔና እናቴን ተገዙኝ!' ባላለበት ተጨባጭ(ምክንያቱም ከአላህ ይልቅ ራሱንና እናቱን ይገዙ ዘንድ አስተምሮ ከሆነ ሽርክ ፈፅሟል እንላለን። ነገር ግን በእስልምና ደግሞ ነቢያቶች ስለማያሻርኩ ይህን እንደማይል ይታወቃል) ገና ለገና 'እንዲህ ተባልኩ' በሚል አሉባልታ የቀረበለትን የአማልደን ጥሪ ገሸሽ ያደርጋል ተብሎ እንዴት ይታመናል? ደግሞስ ሁሉን አዋቂው አላህ 'እኔና እናቴን ተገዙኝ ያልከው አንተ ነህን?' ብሎ ጠየቀው ማለት አላህን ማቅለል አይሆንም ወይ?

ሌላኛው ሐዲስ በሳሂህ አልቡሐሪ335 መፅ 7 ቁ. 2 የሚገኝ ሲሆን። እንዲህ ይነበባል፦ "ከጃቢር ኢብኑ ዐብዱላህ ተዘግቧል፤ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፦ "ከእኔ በፊት ለማንኛውም ነቢይ ያልተሰጡ አምስት ነገሮች ተሰጥተውኛል፦ 1. በአንድ ወር የጉዞ ርቀት ላይ ባለው ጠላት ልብ ውስጥ ፍርሃት በመጣል ድል ተሰጥቶኛል። 2. ምድር ለእኔ የሶላት ቦታ እና የመንጻት መንገድ ተደርጋለች፤ ስለዚህ ከኡማቴ ማንኛውም ሰው የሶላት ጊዜ በደረሰው ቦታ ይስገድ። 3. የጦር ምርኮ ለእኔ ሐላል ተደርጓል፤ ከእኔ በፊት ለማንም ሐላል አልነበረም። 4. ምልጃ ተሰጥቶኛል። 5. ከእኔ በፊት ነቢይ እያንዳንዱ ወደ ራሱ ሕዝብ ብቻ ይላክ ነበር፤ እኔ ግን ወደ ሰዎች ሁሉ ተልኬያለሁ።"

ሌሎች ነቢያቶችም እንደሚያማልዱ እየታወቀ ነቢዩ መሐመድ ተሰጡኝ ብለው ከዘረዘሯቸው 5 ነገሮች አንዱ 'ምልጃ' እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ሙስሊም ምሁራን ብዙም ግልፅ የሆነ ማብራሪያ ባያቀርቡም(የተለመደው ማብራሪያ የእርሳቸው ምልጃ የሚለየው በተፈፃሚነቱ ነው የሚል ነው። መረጃዎች ወደዚህ ድምዳሜ ባያመሩም) ቢያንስ ግን ከዚህ ሐዲስ ነቢዩ መሐመድ አንዳች አይነት የምልጃ ስራን እንደሚሰሩ ማመን ይቻላል።

በዚህ ቦታ የምናየው ሶስተኛው ሐዲስ የሚከተለው ነው። "አቡሑረይራ የዘገበው ነው፦ የአላህ መልዕክተኛ አሉ፦ እያንዳንዱ መልዕክተኛ ለሕዝቡ የሚያቀርበው ሆኖ ተፈፃሚ የሚሆን ምልጃ ተሰጠው። ሁሉም ሲያቀርቡ እኔ ግን በትንሳኤ ቀን ሕዝቤን አድንበት ዘንድ ቆጠብኩት። አላህ ከፈቀደ በአላህ ላይ ሳያሻርክ ለሚሞት ለሁሉም ተከታዮቼ መሆን የሚችል ነው" -(ሙስሊም199 መፅ1 ቁ.397)

አራተኛው ሐዲስ ይህ ነው፦ "አኡፍ ቢን ማሊክ የተረከው ነው፦ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ 'አንድ አካል ከጌታዬ ዘንድ ወደ እኔ መጣና ግማሹን ሕዝብህን ጀነት ከማስገባና ከምትማልድላቸው የቱን ትመርጣለህ?አለኝ። እኔ ምልጃን መረጥኩ።.."

እነዚህ ሐዲሶች የሚያስነሷቸው ስነመለኮታዊ ጥያቄዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምልጃን በተመለከተ ግልፅ የሆነን ትምህርት ይዘዋል። ይኸውም ነቢዩ መሐመድ በፍርዱ ቀን ለሐጢያተኛ ሙስሊሞች እንደሚማልዱ ነው። ስለሆነም  ከቁርአን በተጨማሪ ሐዲሶች በፍርዱ ቀን ነቢዩ መሐመድ ሐጢያተኛ ሙስሊሞችን ወክለው እንደሚቀርቡ ያስረዳሉ ማለት ነው። ይህ ሲባል ብቸኛው አማላጅ ነቢዩ መሐመድ ናቸው ማለት አይደለም።  ከእርሳቸው በተጨማሪ ለአማኞች ማማለድ የሚችሉ ሌሎች አካላትም እንዳሉ ይታመናልና። ከእነዚህም መካከል መላዕክቶች፣ ሌሎች ነቢያቶች፣ ራሳቸው አማኞች/እርስ በእርስ/፣ ሰማዕታት/በጅሀድ ሲዋጉ የሞቱ ሰዎች/፣ ኡለሞች ወይንም የሐይማኖት ምሁራን፣ እንዲሁም መልካም ስራ(ለምሳሌ ፆምና ዘካ) በስተመጨረሻም ራሱ ቁርአን ለአማኞች ይማልዳል።

አልጋዛሊ ማላጆችን በተመለከተ አማኞች ሊቀበሉት የተገባው የሚሉት ይህን ነው፦ "(አማኝ) ነኝ የሚል ሰው በነቢያቶች፣ በኡለሞች፣ በሰማዕታት፣ እንዲሁም በአማኞች ምልጃ ማመን ይኖርበታል።..." --(Watt pg. 78 እና ገፅ 54 ይመ ቅንፍ የእኔ) ፆም እና ቁርአንም ለሙስሊሞች እንደሚማልዱ የሚያሳዩ መረጃዎች አሉን። በተለይ ቁርአንን የሚቀራ ሰው ጀነት እንዲገባ ተደርጎ ለ10 ቤተሰቦቹ የመማለድ ዕድል እንደሚሰጠው ይታመናል (Bah pg. 34)።

## <u>የነቢዩ ምልጃ ልብን የማያሳርፍባቸው ምክንያቶች</u>

እስካሁን በነበረን ውይይት በመልካም ስራቸውም ይሁን፣ በእምነታቸው ጀነት የመግባት ዕድል ያላገኙ ሰዎችን በተመለከተ፣ እስልምና በምልጃ እንደሚድኑ ተስፈ መስጠቱን ተመልክተናል። በተለይ የለመኑትን የማይነሳ የሆነው አላህ የፍጥረታት ቁንጮ በሆኑት በነቢዩ መሐመድ በኩል የሚመጣውን ሰው ሁሉ እንደማያሳፍር ግልፅ ሆኗል።

ከዚህም የተነሳ ይህን አስተምህሮ የሚቀበሉ ሙስሊሞች ሁሉ ከአሏህ በታች(አንዳንዴም በላይ) የዘላለም ዕጣፈንታቸውን በተመለከተ ሲያስቡ በነቢዩ መሐመድ ምልጃ ላይ ተስፋ እንደሚያደርጉም ተመልክተናል።

ታዲያ ከዚህ በታች የምንመለከተው ሙሉ በሙሉ በነቢዩ መሐመድ ምልጃ ላይ የተንጠለጠለው ይህ ተስፋ በእርግጥ ልብን የሚያሳርፍ ነው ወይ? የሚለውን ነው። በመሆኑም ከዚህ በታች ይህን የድነት መንገድ ስለምን ልንቀበለው እንደማይገባ ምክንያታችንን እናስቀምጣለን።

>>. ***የነቢዩ መሐመድን ልመና ያልመለሰባቸው ብዙ ጊዜያት ስላሉ ምልጃቸውን ልንተማመንበት አንችልም፡-*** ከየት እንዳመጡት ባላውቅም፣ ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ የሚጠይቁትን ነገር ሁሉ አሏህ እንደሚፈፅምላቸው ነው የሚያስቡት። የሚከተለውን ስንኝ ያስተውሏል

Please pray for us on Doomsday
Your name is beautifull, you yourself are beautifull, Muhammed!
Your words are accepted near God, the lord
Your name is beautifull, you yourself are beautifull, Mohammed
-- Yunus Emre, Anatolian Minister (ANNEMARIE, pg.117)

ይሁንና ግን ይህ አይነቱ እምነት አንድም ግለታሪካቸውን ካለማንበብ ወይንም ደግሞ 'እውቀት አልባ ከሆነ ድፍን ፍቅር' የሚመነጭ ብቻ ነው። ከዚህ በታች የቀረቡት ማስረጃዎች ግልፅ እንደሚያደርጉት ከሆነ ግን ነቢዩ መሐመድ በተለያዩ ጊዜያቶች ፀሎት አቅርበው ሳይመለስላቸው የቀረባቸው ጊዜያት ነበሩ። የተወሰኑትን ብቻ እንመልከት፡-

በሳሂህ አልቡሐሪ6055 መፅ78 ቁ.85 አንድ ታሪክ ቀርቧል። ኢብን አባስ የዘገበው ነው፡- ነቢዩ መሐመድ መዲና በሚገኝ አንድ መቃብር አጠገብ እያለፉ እያለ በመቃብር ውስጥ የሚሰቃዩ ሰዎችን ጩኸት ሰሙ። በዚህ ጊዜ እንዲህ አሉ 'እነኚህ ሰዎች እየተቀጡ የሚገኙት ቀላል ባይባልም 'ታላቅ ወንጀል/Major sin/' ፈፅመው ግን አይደለም። አንደኛው ሽንቱን ሲሸና ልብሱን ስለነካበት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በሐሜት ስለተሳተፈ ነው'። ይህን ካሉ በኋላ የዘንባባ ዝንጣፊ አስመጥተው ለሁለት በመሰንጠቅ በሁለቱ ሰዎች መቃብር በማኖር ይህን አሉ፡- 'እነህ ዘንባባዎች እስከሚደርቁ ድረስ ምናልባት ቅጣቱን እንዲያቀልላቸው ተስፋ አደርጋለሁ'(ሱናን ኒሳኢ.31 መፅሀ 1, ቁ. 31፤ ሱናን ኒሳኢ.2068 መፅሀ 21, ቁ. 251 ይመ)

በመቃብር ውስጥ እየተቀጡ ላሉት ነፍሳት(11) ቅጣቱ ይቀልላቸው ዘንድ በማለት ነቢዩ መሐመድ ያቀረቡት ምልጃ(ወይንም ያደረጉት ሙከራ) በእርግጠኝነት ሟቾቹን ይጠቅም አይጠቅም እንደሆነ እርግጠኛ አልነበሩም። ይህንንም *'ምናልባት/perhaps/ ቅጣቱን እንዲያቀልላቸው...'* ከሚለው ንግግራቸው እንረዳለን። ይህ ብቻ አይደለም የዚህ ታሪክ ሌላው አስገራሚው ነገር ምልጃቸው ለተወሰኑ ሰዓታት(ቀናት) ብቻ የቀረበ መሆኑ ነው። ይህም ማለት በለስ ቀንቶአቸው ምልጃቸው ቢሰማ ራሱ ተቀጪዎቹ ስቃዩ የሚቀንስላቸው(ስቃዩ ይቀንሳል ተባለ እንጂ ይቆማል እንዳልተባለ ልብ ይሏል?) ዘንባባዎቹ እስከሚደርቁ ድረስ ብቻ ነው። ዘንባቦቹ በሙሉ ሲደርቁ ሰዎቹ ተመልሰው ወደ ነበሩበት ስቃይ ይገባሉ ማለት ነው።

ታሪኩ ላይ አስተያየት ከሰጡ ሙስሊም ምሁራን አንዱ የሆኑት ሙሐመድ ሙስጠፋ የሰጡት አስተያየት ሊጠቅሰት የተገባ ነው፡- "These hadith highlights the seriousness of the sins committed by these two individuals because EVEN THE PROPHET'S Supplication for them would not have a permanent effect, in reducing their punishment" –( Barzakh pg.171 CAPITAL EMPHASIS IS MINE)

---

(11). ቢያንስ አንደኛው ሙስሊም እንደነበር፣ ከተከሰሰበት ክስ ተነስተን ማረጋገጥ እንችላለን። ከላይ እንዳነበብነው የቀረበበት ክስ 'ከሽንት ርኩሰት ራሱን አልጠበቀም' የሚል ነውና። ሽንት ልብስ ላይ ከተንጠባጠበ ያረክሳል የሚለው እስልምና በመሆኑ። ይህ ሰው ሙስሊም እንደነበር ግልፅ ነው። ሌሎች እንዲፈፅሙት አይጠበቅምና

ሙሐመድ ሙስጠፋ የነቢዩ መሐመድ ፀሎት ቋሚ በሆነ መልኩ ከስቃይ የማይገላግል መሆኑን ታሪኩ እንደሚያስተምር መካድ አልቻሉም። ከዚህም የተነሳ 'የነቢዩ መሐመድ ፀሎት እንኳን ቋሚ እረፍት ማስገኘት አልቻለም' ብለው እንዲሉ አስገድዷቸዋል። ይሁንና ይህን ሲያደርጉ፣ ታሪኩ 'የነቢዩ ፀሎት ያልተመለሰው ከማንኛውም ተራ ሰው ፀሎት ያልተለየ ስለሆነ ነው' የሚል ድምዳሜ እንዳያሲዝ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ነው። ጉዳዩን ግለሰቦቹ ከፈፀሙት ሐጢያት ጋር በማያያዝ 'የፈፀሙት ሐጢያት ሀይለኛ/Serious/ ስለሆነ ነው' በማለት ነቢያቸውን ለማስመለጥ ሞክረዋልና።

ከላይ በጠቀስናቸው ሁሉም ሐዲሶች ግለሰቦቹ የፈፀሙት ሐጢያት ተራ አይሁን እንጂ 'ታላቅ ሐጢያት' ከሚባሉት እንደማይመደብ በግልፅ ተብራርቷል። ስለዚህ ብቸኛው ምክንያት የነቢዩ ፀሎት ሙስሊም ወገኖቻችን ከሚያስቡት በተቃራኒው በአላህ ፊት ከተራ ሰው ፀሎት የተለየ ሆኖ ስለማይታይ ነው የሚለው ይሆናል(መሐመድ ሙስጠፋ ሐጢያቶቹን Serious ብለው ይጥሯቸው እንጂ በሐዲሶቹ ታላቅ ሐጢያት እንዳልሆኑ ከሚናገሩት የሐዲሶቹ ምንባባት ጋር ይህ ፍረጃቸው እንዴት እንደሚታረቅ እንዳላብራሩ መታወቅ ይኖርበታል)።

<u>ነቢዩ</u> መሐመድ ለተወሰኑ ቀናት(ሰዓታት)፣ ሊያውም 'ሙሉ በሙሉ ስቃዩን ለማቆም' ሳይሆን ለመቀነስ ያቀረቡት ምልጃ ይመለስ አይመለስ እርግጠኛ አለመሆናቸው ስለዚህ የዚህ ታሪክ ትልቁ ትምህርት ይሆናል ማለት ነው። በይዘቱ ተመሣሣይ ሀሳብ ካለው ከቡሐሪ ሌላኛው ዘገባ ስንዘልቅ የምናገኘውም እውነት ይህንኑ ድምዳሜያችንን የሚያጠናክር ነው፡- "ሰኢድ አል-ኹድሪ እንደተረከው ከሆነ፡- የአቡጧሊብ ስም እርሳቸው ባሉበት በተነሳ ጊዜ ነቢዩ እንዲህ ሲሉ ሰማኋቸው 'ምልጃዬ ምናልባት በፍርድ ቀን ሊጠቅመው ከቻለ ከእሳቱ ጥልቀት ወጥቶ አናቱን የሚያንተከትከው የእሳቱ ዳርቻ ላይ ሊቆም ይችላል"–(ቡሐሪ6564 መፅ8፣ ቁ.153)

አቡጧሊብ በምድር ቆይታው ወቅት እጅግ ይወዳቸው የነበረና፡፡ በተደጋጋሚም ከጠላት ጥቃት ሲያድናቸው የነበረ ባለውለታቸው እንደመሆኑ ርህራሄ ተሰምቷቸው ሊማልዱለት መፍቀዳቸው በራሱ መልካም ነበር። ይሁንና ምንም ያህል ለእርሳቸው ቀና አመለካከት ያለው ቢሆንም ከአላህ ዘንድ ያመጣሁት ነው የሚሉትን እስልምና ለመቀበል ልቡ እሺ አላለለትም ነበር። ከዚህም የተነሳ እስልምናን እስከመጨረሻው እስትንፋሱ ድረስ ሳይቀበል በመሞቱ ነቢዩ አዝነዋል። ተስፋ አለው ብለውም እንዳይፀናኑ ያደረጋቸው ይህ እውነት ነበር።

በዚህም ምክንያት ደግሞ ወዳጃቸውን ሙሉ በሙሉ ከቅጣት እንደማያስጥሉት ጠንቅቀው አውቀዋል። ምናልባት ግን አሉ 'ምናልባት ምልጃዬ በፍርድ ቀን ከጠቀመው.......ከእሳቱ ዳር ሊመደብ ይችላል'።

በዚህ ቦታ አንባቢ ልብ ሊላቸው የሚገቡ ቢያንስ ሁለት ነጥቦች አሉ፡- አንደኛው፡- ምልጃቸው እንኳንና 'ቅጣትን ሙሉ በሙሉ ሊያስቀር'፤ 'ቅጣትን መቀነሱ' ላይ ራሱ እርግጠኛ አለመሆናቸው ነው። ሁለተኛው ነጥብ፡- ለወዳጃቸው ባቀረቡት ተማፅኖ አሏህን ፈራ ተባ እያሉም ቢሆን የጠየቁት ቅጣት እንዲቀንስ ብቻ መሆኑ ነው(12)

በሳሂህ ሙስሊም2890 መፅ54 ቁ.26 ይህ ተፅፏል፡- "ኢብን ሰዕድ ከአባቱ ሰዕድ ኢብን አቢ ወቃስ እንዲህ ሲሉ ዘግበዋል፡- አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ ከአል-ዓሊያህ መጡ። በበኑ ሙዓዊያ መስጂድ በኩል ሲያልፉ ወደ ውስጥ ገቡ፤ ሁለት ረከዓ ሰገዱ፣ እኛም ከእርሳቸው ጋር ሰገድን። ከዚያም ለጌታቸው ረጅም ጊዜ ዱዓ አደረጉ። ከዚያ ወደ እኛ መጥተው እንዲህ አሉ፡- «ጌታዬን ሦስት ነገሮች ጠየቅሁት፤ ሁለቱን ሰጠኝ፣ አንዱን ግን ከለከለኝ። ሕዝቤን (ኡማቴን) በድርቅ እንዳያጠፋቸው ጠየቅሁት፤ ይህንንም ሰጠኝ። ሕዝቤን በመስጠም/በጎርፍ እንዳያጠፋቸው ጠየቅሁት፤ ይህንንም ሰጠኝ። በመካከላቸው እርስ በርስ ጦርነትና ደም መፋሰስ እንዳይኖር ጠየቅሁት፤ *ይህንን ግን አልሰጠኝም።*»

---

(12). የዚህ ምክንያቱ አቡጧሊብ ኢ-አማኝ ስለሆነ ነው ሊባል ይችላል። ግና አሏህ ኢ-አማንያንን የማሳረፍ ዕቅድ/ፍላጎት/ ከሌለው ሲጀምር ስለምን ነቢዩ ቅጣት ይቀንስ ዘንድ ይጠይቁታል? አቡጧሊብ ለመሐመድ ካደረጉት ውለታ ጋር አሏህ ፀብ ባይኖረውም/እንደውም ለመሐመድ መልካም በማድረጋቸው አሏህ እንደሚወዳቸው ግልፅ ነው/፤

ሰዎች እርስ በእርስ እንዳይጠፋፉ መመኘትም ሆነ ይህ እንዲሆን መፀለይ በሰውም ሆነ በፈጣሪ ዘንድ የሚያስመሰግን ደግ ነገር ነው። ነቢዩም ያደረጉት ይህንኑ ነው፣ 'ሕዝቤ እንዳይጠፋፉ ፍቀድ' በማለት ዑመታቸው በሰላምና በፍቅር ይኖሩ ዘንድ ፍቃዱን ነው የጠየቁት።

ይሁንና በሚያስገርም መልኩ ይህን ልመናቸውን አሏህ እንዳልመለሰላቸው ነው የተነገረን። ለምን አልፈቀደም? ለሚለው ምክንያቱን የሚያስረዳ ተጨማሪ ማብራሪያ ባለመቅረቡ ግልፅ ባይሆንልንም። ነቢዩ መሐመድ አንድን ነገር ስለለመኑ ብቻ የሚፈፀምላቸው ነቢይ አለመሆናቸውን ግን ከሐዲሱ ልንማር እንችላለን።

ሌሎችም ሐዲሶች ተመሣሣይ ሀሳብ ይዘዋል። ከእነዚህም መካከል አንዱ ሳሂህ ሙስሊም976 መፅ፤ ቁ.134 ነው። በሐዲሱ መሠረት ነቢዩ መሐመድ ወደ እናታቸው መቃብር በሄዱ ጊዜ የእናታቸውን ድነት በማሰብ ምህረት ያደርግላቸው ዘንድ አላህን በጠየቁት ጊዜ። አሏህ እንዳልፈቀደላቸው የገለፁት '...He did not grant me persmission...' በማለት ነው። "I sought permission to beg forgiveness for my mother, but He did not grant it to me. I sought permission from Him to visit her grave, and He granted it (permission) to me."(የነቢዩ አባትም በጀሐነም እንደሆነ ያውቋል?)

የነቢዩ መሐመድ እናት እንደ አቡጧሊብ የእስልምና መልዕክት ደርሷቸው አልቀበልም ብለው አይደለም ያለፉት። ከዚህ ይልቅ እስልምና ገና ለሰው ልጅ ባልተዋወቀበት ዘመን ያለፉ ናቸው(አሕለል ፊጥራህ)። ሆኖም 'እስልምና ባልተዋወቀበት ዘመን' መኖራቸው፣ እንዲሁም 'የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ' የሆኑትን ነቢይ መውለዳቸው እንኳን ከግምት ሳይገባላቸው(በሕግ ቋንቋ - እንደ ቅጣት ማቅለያ ሳይወሰድላቸው) በጀሐነም እሳት እንዲከሰሉ መደረጉን ነው ያነበብነው(13)። ነቢዩም ቢሆኑ እናታቸው በጀሐነም የሚደርስባቸውን መከራ እያሰቡ አንጀታቸው ይቁሰል እንጂ። እያለቀሱ ስለለመኑ ብቻ ጥያቄያቸው እንደማይመለስላቸው ነበር የተነገራቸው።

ነገርን ላለማንዛዛት ማስረጃውን እዚህ ስንቋጨው፦ ነቢዩ መሐመድ ልመናቸው ያልተሰማባቸውን ሌሎች ማስረጃዎችም መጥቀስ እንደምንችል እየገለፅን። ከሁሉም ማስረጃዎች የሚገኘውን ትምህርት ላይ አፅንኦት እንዲደረግ ግን እናሳስባለን። ይኸውም ነቢዩ መሐመድ እንደማንኛውም ሰው የተሰማላቸው ፀሎቶች እንዳሉ ሁሉ ያልተሰሙላቸው ፀሎቶችም መኖራቸው ፀሐይ የሞቀው ሀገር ያወቀው ጉዳይ ነው። ስለዚህም ደግሞ ከሌሎች ሰዎች በተሻለ ልመናቸው እንደሚሰማ ማረጋገጫ በሌለን ነቢይ ላይ ትምክህታችንን መጣሉ አዋጪ ሆኖ አይሰማንም።

---

በኢ-አማኒነታቸው የተነሳ ግን ሊያሳርፉቸው ካልፈለገ፣ ከዚህ የአሏህ ፍላጎት ጋር በተቃረነ መልኩ ነቢዩ አቡጧሊብ ቅጣቱ ቀንሶላቸው እንዲያርፉ ለምን ፈለጉ? ከአሏህ ፍላጎትና ከነቢዩ ፍላጎትስ የቱ ሊፈፀም ይችላል? ከነቢዩ ምልጃ የተነሳ አሏህ የኢ-አማንያንን ቅጣት የሚቀንስ ከሆነ(ይህ ሐዲስ የሚያስተምረው ይህን ነውና) ነቢዩ መሐመድ ለሌሎች ኢ-አማንያንስ ይህን የመሰለ ምልጃ ሊያቀርቡ ይችላሉ ወይ?(ካልቻሉ ለምን? ከቻሉ ደግሞ የነቢዩ ምልጃ ሙስሊሞችን ብቻ/ከባድ ሐጢያት የፈፀሙትን/ ነው የሚጠቅመው የሚለው መሠረታዊው አስተምህሮ እንዴት ይገናዘባል

(13). የነቢዩን ወላጆችን ዕጣ ፈንታ በተመለከተ ሙስሊም ምሁራን በዘመናት መካከል የተለያዩ አቋሞችን አንፀባርቀዋል። ቢሆንም ግን ጀሐነም መግባታቸው ሳሂህ በሆኑ ሐዲሶች የተረጋገጠ ስለሆነ። በዚህ ፅሁፍ ይህ አመለካከት ተንፀባርቋል

>>. ***የምልጃ አስተምህሮ መፈፀም የሚገባውን ፍትህ የሚያዛባ በመሆኑ ከአምላክ ያልሆነ ነው፡-*** የምልጃ አስተምህሮ አላህ የደነገገውን ውሳኔ መቀልበስን የሚመለከት በመሆኑ ወይንም ደግሞ መደንገግ የነበረበትን ቅጣት የሚያስቀር በመሆኑ አምላክን ኢ-ፍትሃዊ የሚያደርገው ነው። ኢማሙ አቡ ሐኒፋ በአንቀፀ ሐይማኖታቸው እንዲህ ማለታቸው ታውቋል፡-

"....Intercession of our prophet on behalf of believers **who have** committed Sins, even great sins *and* **deserve punishment** is certainly real" –( Watt pg. 66 አፅንኦት የእኔ)።

እንዲሁም ከሐገራችን ታዋቂ ሙነሺዶች አንዱ የሆኑት ፉአድ ሙሐመድ 'አላሁ ማሊከሙሉቅ' በተሰኘው መንዙማቸው ለማንም የማይቻለው የአላህን ፍርድ መቀልበስ ለነቢዩ ሲሆን እንዴት እንደሚሰራ ያሳዩት እንዲህ በማለት ነው፡-

ፍርዱ የማይሻር የማይቀር
ለአንድ ሰው እንጂ ለዘይነል በሸር
የቂያማ ቀን ሁሉም ሲሸሽ
ለሙስጠፋ ነው የሚለው እሺ (14)

በዋናው እስላም/Mainstream Islam/ ከመናፍቅ የሚቆጠሩት ሙታዚላውያን የምልጃ አስተምህሮ የአላህን ፍትሃዊነት ጥያቄ ውስጥ ይጥለዋል ማለታቸው ከምን የተነሳ እንደሆነ አሁን ግልፅ የሆነ ይመስለኛል። 'ድምፅን በድምፅ የመሻር' ስልጣን ያላቸው አስመስሎ ነቢዩ መሐመድን ሰማይ የሚሰቅላቸው ይህ አስተምህሮ በእርግጥ ከተውሂድ ፅንሰ ሀሳብ ጋር የማይሄድ በመሆኑ ሊወገዝ የተገባው ነው።

>>. ***<u>ምልጃ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ከመቀጣት ስለማይድኑ</u>***፡- በሚያስገርም መልኩ እስልምና በመሐመድ ምልጃ ከቅጣት ይድናሉ የሚላቸው ሰዎች ለሐጢያታቸው ተመጣጣኝ ቅጣት የሚቀጡ ናቸው። ለምሳሌ በአልቃዲ መሠረት ሙስሊም ሐጢያተኞች ለ1000 ዓመት በጀሐነም ከተሰቃዩ በኻላ ወደ አሏህ ይጮሁና፤ አላህም እስቲ የተፈጠረውን አጣሩ ብሎ ገብርኤልን ወደ ጀሐነም ልኮት በስተመጨረሻ በመሐመድ አማካኝነት ከጀሐነም እንደሚወጡ ተነግሯል(Nerina pg. 159 በተጨማሪም Lange pg 8 ይመ)

ማስረጃ እናክል፡- የሐንባሊ የእምነት አንቀፅ ይህን ይላል፡- "የትንሳኤ ቀን ምልጃ የተረጋገጠ እውነት ነው። ሰዎች ገሀነም እንዳይገቡ ለሌሎች ይማልዳሉ። በአማላጆች ምልጃም በገሐነም አላህ ለፈቀደው ጊዜ ያሕል *<u>ይሰቃዩ ዘንድ</u>* የገቡ ሰዎች ተመልሰው ይወጣሉ..." –(Watt pg.36)

ሳሂህ በሆነ የሱናን አቡዳውድ4740 መፅ42 ቁ.145 ሐዲስ ይህን እውነት እንደሚከተለው ያቀርበዋል። ኢምራን ሁሴን በዘገበው መሠረት "በነቢዩ መሐመድ አማካኝነት *<u>ከጀሐነም እንዲወጡ የሚደረጉት ሰዎች</u>* ጀነት የሚገቡ ሲሆን። ጀሐነማዊያን/ Jahannamis/ ተብለው ይጠራሉ"ይላል።(በተጨማሪም ቡሐሪ6566 መፅ81 ቁ.155 ይመ)

ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች በሙሉ አሏህ 'ነቢዩ መሐመድ የሚባል አማላጅ አላቸው' ብሎ ሙስሊሞችን ከቅጣት እንደማያድናቸው የሚያስረዱ ናቸው። በተቃራኒው በሰራነው ሐጢያት አይነትና መጠን በገሐነም ከማበደባየት የሚከለክለው አንዳችም አካል ወይንም ሀይል እንደሌለ ያስመሰከረባቸው ታሪኮች ናቸው። በአንዳንድ ምንጮች መሠረት ከሆነ እንደውም ምልጃቸው የሚፈቀደው አላህ ሐጢያተኛ ሙስሊሞችን *<u>'ከሰል እስኪመስሉ ድረስ...'</u>* በጀሐነም ከጠበሳቸው በኋላ ነው(ሙስሊም 185 መፅ1 ቁ.364 እንዲሁም ኢብነ ማጃህ4309 መፅ37 ቁ.210 ይመ)።

---

(14). https://youtu.be/sdXwU4YoyWc?si=C6DT_KNkSwfK9hTM

ይህን በመሰለው ዐውድ ውስጥ ደግሞ ነቢዩ መሐመድ የተፈረደን ፍርድ ወይንም የተላለፈን ቅጣት መቅለበሳቸውን(መቀነሳቸውን) የሚያሳይ አንዳችም ማስረጃ ስለሌለ አላህ አይቀጣ እንጂ ከቁጣው የመገላገል አቅም እንደሌላቸው ማወቅ ተችሏል። ይህም 'የአሕያ ባል ከጅብ አያስጥልም' የሚለውን ብሂል የሚያስታውስ ነው።

>>. ***<u>አስተምህሮው ሰዎች ሐጢያትን እንዳይፈሩ ስለሚያደርግ፦</u>*** <u>የምልጃ አስተምህሮ ስህተት ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱና ምናልባትም ትልቁ ሰዎች ሐጢያትን እንዳይፈሩ የማድረግ አቅም ያለው መሆኑ ነው። ሰዎች ላጠፉት ጥፋት ወይንም ለፈፀሙት ሐጢያት ይቀጣሉ የሚለውን ርቱዕ አምላካዊ አስተምህሮ ባጣጣለ መልኩ ሐጢያተኛ ሰዎች 'ጠፍተው አይጠፉም' ወይንም ከነጭራሹ ጉዳት አያገኛቸው የሚለው ይህ አስተምህሮ ሰዎች ቅጣትን ፈርተው ራሳቸውን በመግዛት እንዳይመላለሱ የማደፋፈር ጠባይ ያለው ነው። እስቲ የአል-ዒሃዊን ንግግር ልብን እንበለው፦</u>

"ትልቅ ሐጢያት የሰሩ ሰዎች በገሐነም መግባታቸው እርግጥ ነው። ሆኖም ንስሀ ባይገቡም እንኳን የአንድ አምላክ ተከታይ/ Monotheist/ ከሆኑ ቆይታቸው ጊዜያዊ ነው።.....እነዚህን አላህ ከምሕረቱ የተነሳ *<u>እንዲሁም አላህን በሚገዙ ሰዎች ምልጃ የተነሳ ከጀሐነም አውጥቶ ጀነት ሊዶላቸው ይችላል</u>*"(Watt 'Islamic creeds...' pg.54

<u>አልዒሃዊ የነቢዩ ምልጃ አንድን ሙስሊም ሐጢያተኛ '....ንስሀ ባይገባም እንኳን' ሊታደገው እንደሚችል ያቀረቡት ትምህርት ግልፅ በሆነ መልኩ ከግብረገብ መርሆ ያፈነገጠ ነው። ሙስሊም ይሁን እንጂ አንድ ሰው የነቢዩ አማላጅነት ስለሚያድነው ሐጢያት ሰራም አልሰራም በድነቱ ላይ የሚያስከትለው ችግር የለም ከሚለው የአልዒሀዊ ትምህርት ማንም ቢሆን ሐጢያትን መራቅ እንደሚኖርበት የሚያሳይ ድምዳሜ ሊያወጣ አይችልም። የዚህም ምክንያቱ የነቢዩ አማላጅነት ለሐጢያት ዋስትና ሆኖ በመቅረቡ ነው።</u>

በደቡብ ኤዥያ <u>ታዋቂው</u> የግጥም ደራሲ Mir Taqi Mir(d. 1810) እንዲህ ሲል ያወረደው ስንኝም ይህን የሚያጠናክር ነው፦

> Why do you worry, O Mir, Thinking of your black book?
> The person of the seal of the prophets is a guarantee for your salvation? –(15)

>>. ***<u>ምልጃቸው ለማን እንደሚሆን ማወቅ ስለማይቻል፦</u>*** በተለያዩ ሐዲሶች መሠረት የነቢዩ መሐመድ ምልጃ በዋናነት ከባድ ወንጀል/Major Sin/ ለፈፀሙ እንደሚውል ያየን ቢሆንም። ከዚህ በታች እንደምንመለከተው ግን ሐጢያትን/ግፍን/ በእንስሳ ላይ እንኳን የፈፀሙ ሰዎች የነቢዩ መሐመድ ምልጃ እንደማይደርሳቸው እንረዳለን። ቡሐሪ ቅፅ2 መፅ24 ቁ.485 ላይ የምናገኘው ሐዲስ እንደሚከተለው ይቀርባል፦ ነቢዩ እንዲህ ብለዋል 'በትንሳኤ ቀን ግመሎች እጅግ ጤነኛ ሆነው ወደ ባለቤቶቻቸው እንዲመጡ ይደረጋል። ከዚያም ዘካቸውን አጉድሎባቸው ከሆነ በእግራቸው እንዲረግጡት ይደረጋል። በተመሣሣይ መልኩ በጎችም እጅግ ጤነኛ ሆነው ወደ ባለቤቶቻቸው እንዲመጡ ይደረጋል። ከዚያም ዘካቸውን አጉድሎባቸው ከሆነ በእግራቸው እንዲረግጡትና በቀንዳቸውም እንዲወጉት ይደረጋል። ከዚያም ነቢዩ እንዲህ አሉ 'አንደኛው መብታቸው ሲታለቡ ከፊታቸው ውሃ መኖር ይኖርበታል። ከእናንተ መካከል ማንም በትንሳኤ ቀን የሚጮህን በግ ተሸክሞ ወደ እኔ እንዲመጣ አልፈልግም። ከዚያም ይህ ሰው 'የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ እባክህን አማልደኝ?' ቢለኝ የምመልስለት 'ልረዳህ አልችልም የአላህን መልዕክት ነግሬህ ነበርና' የሚል ነው" በተመሣሣይ መልኩ ከእናንተ መካከል ማንም በትንሳኤ ቀን የሚጮህን ግመል ተሸክሞ ወደ እኔ እንዲመጣ አልፈልግም። ከዚያም ይህ ሰው 'የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ እባክህን አማልደን?' ቢለኝ የምመልስለት *<u>'ልረዳህ አልችልም የአላህን መልዕክት ነግሬህ ነበርና' የሚል ነው"</u>*

---

(15). Annemarie, 'And Muhammed...' pg. 99 በግጥሙ Black book የተባለው ክፉ ስራ የሚመዘገብበትን መዝገብ ነው?

በታሪኩ መሠረት በእንስሶች ላይ እንኳን ግፍ የፈፀመ ሰው(ሐቃቸውን የከለከላቸው) የነቢዩን ምልጃ የማይጠቀም ከሆነ፤ በሰው ልጅ ላይ ግፍ የፈፀመም ሰው የነቢዩ ምልጃን እንደማይጠቀም በአዕምሮ(በሕሊና) ልንረዳ እንችላለን።

ይህ እውነት እንዳለ ሆኖ በምንባቡ ላይ ትኩረት ልንሰጠው የተገባ ሐረግ አለ። ይኸውም *'....የአላህን መልዕክት ነግሬህ ነበርና'* የሚለው ነው። ይህም ማለት የአላህ መልዕክት ደርሶህ/ተነግሮህ/ ሳለ ልትጠብቀው ሲገባ ባለመጠበቅህ የተነሳ ለደረሰብህ ነገር ዋስትና አልሰጥህም ማለታቸው ነው። በሌላ አነጋገር ዋስትናዬ/አማላጅነቴ/ የአላህ ህግ ደርሷቸው ለሚጠብቁት ብቻ ነው እንደማለት ነው። ይህም ማለት ምልጃቸው 'የአላህ መልዕክት ተነግሯቸው' ላልፈፀሙ ሐጢያተኛ ሙስሊሞች አይሆንም ማለት ነው። ታዲያ ምልጃቸው የሚመለከተው ማንን ነው? ቢባል ቢያንስ ለፃድቃን እንደማይሉን ተስፋ አድርገን 'ለማን እንደሆነ እንጃ?' ብለን እንመልሳለን።

>>. ***ነቢዩ መሐመድ ሐጢያት ያለባቸው በመሆኑ የምልጃን መስፈርት ሊያሟሉ አይችሉም፡-*** በተለምዶ 'የምልጃ ሐዲስ' ተብሎ የሚታወቀው ሐዲስ ሐጢያት አልቦነት ለምልጃ ዋናው መስፈርት እንደሆነ እንደሚያስረዳ ተመልከተናል። የነቢዩ መሐመድ ሕይወት ደግሞ በሐጢያትና በግፍ የተሞላ እንደመሆኑ(16) ይህን መስፈርት በብቃት ያልፉታል ብለን አናምንም።

በቀን ከ70 ጊዜ በላይ(አንዳንድ ሐዲሶች ከ100 ጊዜ በላይ ነው ይላሉ) በአላህ ፊት ንስሀ የሚገቡ(ቡሐሪ8:3; 75; 213; 319 ይመ)፤ ለቁጥር የሚታክቱ ተግሳፆችን ከአላህ የተቀበሉ ነቢይ፣ ፍፁም ንፁሕ/Perfectly sinless/ መሆንን በሚጠይቀው በዚህ አገልግሎት የመሳተፍ ሞራል ሊኖራቸው አይገባምም/አይችልምም/። ስለዚህም ምልጃቸውን መጠራጠራችን ሲበዛ ምክንያታዊነት ነው ማለት ነው።

>>. ***እንዲታደጉኝ እየጠበቅኳቸው የእኔን ትድግና መጠበቃቸው፡-*** የሚከተሉትን ማስረጃዎች ያጢኑ፡- በሞሮኳዊው ሱፊ አል-ጃዙሊ የተፃፈውና ለነቢዩ ውዳሴን የሚሰጡ ከሆኑ መመሪያዎች በስፋት ጥቅም ላይ የሚገኘው 'Dala'il al-Khairat' ሙስሊሞች ምን ብለው ነቢዩ ያማልዳቸውና ምልጃውም ቅቡልነት እንዲያገኝ አላህን መለመን እንዳለባቸው ሲያስተምር ይህን ብሏል፡- "አሏህ ሆይ ነቢያችንን እጅግ ታማኝ ተናጋሪ፣ ጠያቂ፣ እና ከአማላጆችም የመጀመሪያው እንድታደርገው። እንዲሁም ምልጃቸው ተቀባይነት ከሚያገኙላቸው ሁሉ በላይ ሞገስ እንድትሰጠው እንለምንሀለን። በተጨማሪም ሁሉንም የዑማውን አባላቶች የሚያካትት ተቀባይነት ያለው አማላጅ እንድታደርጋቸው እንጠይቅሀለን።" – (Annemarie,' pg. 97)

አቡሙሳ በዘገበው አንድ ሐዲስ ደግሞ ነቢዩ ይህን ብለዋል፡- "ምንዳ ታገኙ ዘንድ ማልዱልኝ። አላህ የነቢዩን ቃል ይደነግጋል" — (አቡዳውድ5131 መፅ43 ቁ.359)።

አማላጅ ያስፈለገው እንኳን ለሌላው ቀርቶ ራሳችንን እንኳን ከጥፋት የምናድንበት አቅም የለንም(በአምላክ ፊት ብቁ የሚያደርግ ሞገስ የለንም) በሚል እምነት ቢሆንም። ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች እንደምናስተውለው ግን፣ ነቢዩ መሐመድ ራሳቸው 'ሞገስ ላላገኝ እችላለሁ' የሚል ፍርሀት እንደነበረባቸው ነው። ይህንንም ለአማላጅነት እንድሾም ማልዱልኝ በሚለው ተማፅኖአቸው ገልፀውታል። ገንዘብ እንዲያበድረኝ/እንዲሰጠኝ/ የምጠብቀው ሰው ለራሴ ቸግሮኛል እኔ ራሱ ከአንተ ልበደር እያሰብኩ ነው እንደሚለው መሆኑ ነው እንግዲህ። የእኛን ልመና እንደሚሹ እየታወቀ 'እኒህ ነቢይ አላህን ተለማምነው ከጀሐነም ያወጡኛል!' ብሎ ማለት ደግሞ ራስን እንደማታለል ስለሚቆጠር 'ምልጃቸውን ልንጠረጥር እንገደዳለን' የሚለው አቋማችን ሆኖ ይዘልቃል።

---

(16). ነቢዩ መሐመድ ሐጢያት የለባቸውምን?' በሚል ርዕስ ከዚህ ቀደም የፃፍኩት ፅሁፍ የነቢዩ መሐመድ ሕይወት እንዴት በሐጢያት የተሞላ እንደሆነ ስለሚያሳይ ጋበዝኩ https://t.me/realsahih/819

>>. ***<u>አላህ ምልጃን የፈለገበት ምክንያት ግልፅ ስላልሆነ፡-</u>*** ይህም ማለት በራሱ መፈፀም የሚችለውን ነገር ስለምን በሶስተኛ ወገን በኩል ማስፈፀም እንዳስፈለገው ግልፅ ስላልሆነ። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ክፉ ስራቸው እኩል ሆኖባቸው ጀነትም ጀሐነምም መግባት ሳይችሉ በመካከለኛ ስፍራ እንዲሰፍሩ የሚደረጉ ነፍሳትን(Wahid pg. 181)፣ እንዲሁም ከጀሐነም የሚያወጣቸው አማላጅ ያላገኙ/የሌላቸው/ ሰዎችን(<u>Watt pg. 78)</u> አላህ ያለ አማላጅ በፀጋው/grace/ ብቻ ምህረት አድርጎላቸው ጀነት ከቶአቸዋል። ይህ ከሆነ ደግሞ በምልጃ ይድናሉ የሚባሉትንም ነፍሳት በተመሣሣይ መልኩ መማር እየቻለ፣ በመሐል አማላጅ የሰነቀረበት ምክንያት ስሜት አይሰጥም። ስለሆነም ከጅምሩ አማላጅ ያስፈለገበት ምክንያት አሳማኝ አይደለም።

>>***<u>. ሕግን መፈፀም ላለቻሉት ሕግን መስፈርት ያደረገ በመሆኑ፡-</u>*** መድሐኒት የሚያስፈልገው ለታመመ ሰው ብቻ እንደመሆኑ። ምልጃቸው ሐጢያትን ለሰሩና ከዚህም የተነሳ በአላህ ፊት ያለ አማላጅ ሞገስ/ተቀባይነት/ ማግኘት ለማይችሉ እንደሆነ ግልፅ ነው። ከላይ ስንጠቅሳቸው በነበሩ ሐዲሶችም በተደጋጋሚ ያየነው ሐረግ ምልጃቸው 'ለሐጢያተኛ ሙስሊሞች' እንደሆነ የሚጠቁም ነው። እነዚህ ሙስሊሞች ደግሞ ሲጀምርም ምልጃ ያስፈለጋቸው ሕግን ስላልፈፀሙ/ወንጀል ስለሰሩ/ ነው። ታዲያ ለእነዚህ ሰዎች ሌላ ተጨማሪ ሸክም የሚሆንባቸውን ሕግ በመስጠት ምልጃን ለማግኘት እንደ መስፈርት አድርጎ ማቅረብ የጤና ነው? በአርግጥ አይደለም።

ሕግን መፈፀም ቢችሉማ መጀመሪያውኑም ለሕግ ተላላፊዎች የሚሆነው ምልጃ ባላስፈለጋቸው ነበር። እዚህ ሀሳብ ላይ ሆነን ልናነሳው የተገባው ጥያቄ፡- እነዚህ ሰዎች ይህን የተሰጣቸውን ትዕዛዝ/ሕግ/ ባይፈፅሙ ዕጣፈንታቸው ምን ይሆናል? የሚል ነው። እነዚህን ሐዲሶች እናጢናቸው እስቲ፡- "አቡሁረይራ በዘገበው መሠረት 'የአሏህ መልክተኛ ሆይ የእርሶን ምልጃ በዕለተ-ቂያማ የሚያገኘው ዕድለኛው ሰው ማነው? ብዬ ጠየቅኳቸው። ሲመልሱም፡- ሐዲሳትን ለማወቅ ካለህ ጉጉት የተነሳ ማንም ይህን ጥያቄ በመጠየቅ እንደማይቀድምህ አስብ ነበር። ዕድለኛው ሰው 'ከልቡ/Sincerely/ ከአላህ በቀር የሚመለክ ማንም የለም' ብሎ የመሰከረ ነው" --ቡሐሪ9 መፅ3 ቁ41(ቡሐሪ6558 መፅ81 ቁ147)

ሌሎች እስላማዊ መረጃዎችን ሳያገናዝብ ይህን ብቻ ሐዲስ የተመለከተ ሰው ከነቢዩ ምልጃ ለመጠቀም ሸሃዳን መወጣት ብቻ በቂ ነው ብሎ ሊያስብ ይችላል። ነገር ግን ይህን ድምዳሜ እንዳንይዝ የሚያደርጉ ምክንያቶች አሉን። የመጀመሪያው በሳሂህ አልቡመሪ99 መፅ3 ቁ.41 ላይ የነቢዩን ምልጃ ለማግኘት የቀረበው መስፈርት 'ከአላህ ውጪ የሚመለክ ማንም የለም ብሎ ማለትና ጥቂትም ቢሆን መልካምነት በልቡ ያለ' ወደሚል ማደጉ ነው። ስለዚህ ሸሃዳ ብቻውን ፋይዳ የለውም ማለት ነው። ከዚህ ጋር በሚስማማ መልኩ ኢማሙ አልጋዛሊ 'Mishkat Al Anwar' ላይ ሲያትቱ 'ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም' የሚለውን አዋጅ አለማውያንና ክፉ ሰዎች ጭምር ሊናገሩት እንደሚችሉ ከገለፁ በኻላ። ነገር ግን ይላሉ 'ነገር ግን ይህ አዋጅ መልካምን ወደ መስራት እስካልመራ ድረስ ብቻውን ከጨለማ ወደ ብርሀን ሊያወጣ አይችልም' ነበር ያሉት(17)። ስለዚህ ምልጃቸው መልካም ስራን እንደ መስፈርትነት ጠይቋል ማለት ነው። እንቀጥል፡-

ጃቢር ቢን አብዱላህ በዘገበው ሐዲስ ነቢዩ ይህን ብለዋል፡- 'Whoever says when he hears the call to the prayer: "Allahumma Rabba hadhihid-da'watit-tammah was-salatil-qa'imah, ati Muhammadanil-wasilata wal-fadilah, wab'athhu maqaman mahmudanilladhi wa'adtah (O Allah, Lord of this perfect call and the prayer to be offered, grant Muhammad the privilege (of intercession) and also the eminence, and resurrect him to the praised position that You have promised)," *<u>my intercession for him will be permitted on the Day of Resurrection</u>*.'" –(ኢብን ማጃህ722 መፅ3 ቁ.17)

(17). Marco pg.136 በተጨማሪም በኢ.ሕ.ያ.እ ኢሉም ዲን ላይ 'ልብን ሳያፀዱ ሸሃዳ መባሉ ብቻውን ፋይዳ የለውም' ብለዋል ኢ.ሕ.ያ.እ ገፅ 505

አብዱላህ ቢን አምር አልአስ በዘገበው ሌላ ሐዲስ ደግሞ፡- “When you hear the Mu'adhdhin, repeat what he says, then invoke a blessing on me, for everyone who invokes a blessing on me will receive ten blessings from Allah; then beg from Allah al-Wasila for me, which is a rank in Paradise fitting for only one of Allah's servants, and I hope that I may be that one. *If anyone who asks that I be given the Wasila, he will be assured of my intercession*.” – (ሙስሊም384 መፅ4 ቁ.13)

ከላይ በቀረቡት ሁለት ሐዲሶች ደግሞ ምልጃቸውን ለማግኘት ከመልካም ስራ በተጨማሪ የተጠቀሱትን ፀሎቶች ለመሐመድ ማድረስ መስፈርት ሆኖ ቀርቧል።

ሌላው በዚህ ቦታ መረሳት የሌለበት ነጥብ ምልጃቸውን ለማግኘት በመስፈርትነት የቀረበው ሸሃዳ አንድን ሰው ትክክለኛ ሙስሊም ያደርገዋል ተብሎ እምነት የማይጣልበት መሆኑ ነው። ይህም ሲባል ሙስሊም ምሁራን የአላህን አንድነት ብቻ መመስከር/ማመን/ ሙስሊም ለመሆን በቂ መስፈርት ነው ብለው የማያምኑ ስለሆነ ነው። በዋናው እስላም ተቀባይነት ያለው ሸሃዳ ከአላህ አንድነት በተጨማሪ የነቢዩ መሐመድንም የአላህ ነቢይነት የሚገልፀው ነውና። አልጋዛሊ በዚህ ረገድ የሚሉት ይህን ነው “የአላህን አንድነት ብቻ የሚያፀድቀው ሐረግ የነቢዩ መሐመድን ነቢይነት ማፅደቅ ካልተጨመረበት በቀር ጎዶሎ ነው” (Watt pg.76)የቀረበው

መስፈርት በቂ አለመሆን እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ ከቀረበው ውይይት የተገነዘብነው ቁምነገር ሕግን መፈፀም የማይችሉ ሰዎች የነቢዩን ምልጃ ለማግኘት እምነት፣ ምስክርነትና መልካም ስራ እንደሚጠበቅባቸው ነው። ይህ ግን ከምልጃ ፅንሰሀሳብ ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ልንቀበለው አይገባም።

>>. ***አስተምህሮው ከተውሂድ የሚያጣላን ስለሆነ፡-*** የምልጃ አስተምህሮ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ሁሉ የከፋው አንዱን አላህን ብቻ ከሚያስመልከው ተውሂድ የሚያወጣን መሆኑ ነው። ይህ በብዙ መልኩ የሚገለጥ ሲሆን። አንድም ከአላህ ይልቅ ያማልደኛል ያልነውን አካል/በዚህ ዐውድ መሐመድን/ እንድንወድ በማድረጉና በሌላ መልኩ ከአላህ ይልቅ አማላጅ ነው ብለን በሾምነው አካል ላይ እንድንታመን ስለሚያደርግ ነው። በሰራሁት መጥፎ ስራ የተነሳ ከሚፈረድብኝ ቅጣት ነቢዩ ይታደጉኛል(ወይንም ቅጣቴን ያሳጥሩልኛል) ብሎ እያመነ አንድ ሰው ከአላህ ይልቅ ነቢዩ መሐመድ አለመውደድ ወይንም ከአላህ ይልቅ በነቢዩ ላይ እምነቱን አለመጣል አይችልምና።

ገጣሚ፣ የሕግ ምሑርና ፈላስፋ እንዲሁም የፓኪስታን መንፈሳዊ አባት ከሚባሉት መሐመድ ኢቅባል(d.1877 – 1935) ያገኘነው ስንኝ ይህን ትምክህት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። እንዲህ ይላል

We trust in him/Muhammed/, at the day of judgment
And in this world too he is our protection
Annemarie pg.258 ቅንፍ የእኔ

## >>. *የምልጃ አስተምህሮ ጣዖትን ለማምለክ በር ከፋች ስለሆነ፡-*

የምልጃ አስተምህሮ አምላክ ከእኛ በእጅጉ የራቀ ነው፣ ከእኛ ይልቅ ፃድቃንን/ነቢያቱን/ ነው የሚሰማው የሚል ስጋት የሚወልደው የመፍትሄ መንገድ ነው። ይሁንና ይህን ሐሳብ የሚያፈርሱ የቁርአን ምንባባት እዚህም እዚያም ተገኝተዋል። አንደኛው በሱረቱ ጋፊር 60 የሚገኘው ሲሆን እንዲህ ቀርቧል፡- ‘ጌታችሁም አለ «ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና። እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ።’

በተጨማሪም በሱረቱል በቀራ 186 እንዲህ የሚል ሀሳብ እናገኛለን፡- ‘ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፡- እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና፡፡’

ያለ መካከለኛ/አማላጅ/ ባሮቹን ከማይሰማና ከማይረዳ አካል ይህን የመሰለው ምክር አይገኝምና። በነዚህ ክፍሎች አላህ እያለ ያለው በቀጥታ ወደ እኔ ብትጮሁ ልሰማችሁ እንዲሁም ችግራችሁንም ልፈታ ፈቃደኛ ነኝ ነው።

ይህም ማለት በአማላጅ የሚያምኑ ሰዎች እንደሚያስቡት አላህ ለባሮቹ እሩቅ ያልሆነና፣ በተቃራኒው ለባሪያው ከደም ስሩ የበለጠ ቅርብ የሆነ ነው ማለት ነው። በመሆኑም ልክ ነቢያቱን/ፃድቃኑን/ እንደሚሰማው ሁሉ ተርታ ባሮቹን የሚሰማ እንደሆነ ማወቅ ይቻላል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፣ ይህን የመሰለውን ምክር ችላ በማለት በአላህ ፊት ተራዳዒ ሊሆን የሚችልን አካል ለራሳቸው የሚሾሙ አካላት ሊያውቁት የሚገባው ሐቅ፤ በዚህ ልምምዳቸው አውቀውም ይሁን ሳያውቁት በአላህ ፊት እያሻረኩ/እያጋሩ/ መሆኑን ነው። ነቢዩ መሐመድ በፍርዱ ቀን ከሚገለጠው ቁጣ/ከሚወሰንብን ውሳኔ/ አላህን ተለማምጦ ያድነናል ማለት በእርግጥ ተስፋን በፍጡር ላይ ማድረግ እንደመሆኑ በቀጥታ ከተውሂድ አስተምህሮ ጋር ያጋጫል።

እዚህ ጋር እንዲህ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡- እኛ ነቢዩ መሐመድ አምላክ ናቸው፣ አዳኝ ናቸው፣ ጌታ ናቸው......ወዘተ ባላልንበት ተጨባጭ እንዴት ሆኖ ነው፤ በአላህ ፈቃድ በዕለተ ቂያማ/በውሳኔው ቀን/ ያማልዱናል ማለታችን ሽርክ ሊሆን የሚችለው?

ይህን ጥያቄ ለሚያነሱ ወገኖቻችን የምናቀርበው አፀፋ። እኛም ቢሆን ነቢዩ መሐመድን ጌታ ነው፣ አምላክ ነው ብላችኋል አልወጣንም። ነገር ግን ሽርክ አንድን አካል ጌታና አምላክ ብሎ ማለት ብቻ ስላልሆነና። ከአላህ ውጪ የሆነን አካል ይረዱኛል፣ ከመከራዬ ይታደጉኛል፣ ያድኑኛል ብሎ ማመንም ሽርክ ስለሆነ አጋርታችኋል እንላቸዋለን።

ፐ/ር ኢማም ዩሱፍ አልቀረዳዊ ‘ተውሒድ ይዘቱና ሚናው’ በሚል ርዕስ ባስነበቡት መፅሀፋቸው፣ አሏህ በተደጋጋሚ በማጋራታቸው የተነሳ ይገስፃቸው የነበሩ የጥንት አረቦች ጣዖቶቻቸውን ሲያመልኩ በግልፅ ጌታና አምላክ ናቸው ብለው ሳይሆን ‘አማላጆቻችን ናቸው’ ብለው እንደሆነ ባስታወሱበት ቦታ ይህን የተነሳውን ጥያቄ የሚመልስ ሀሳብ ስለሚገኝበት እርሱን መጋበዙ ጠቃሚ ይሆናል። እንዲህ ነበር ያሉት፡- “የምንማፀናቸውና እገዛቸውን የምንከጅለው ሙታን አማልክት ናቸው ብለን አናምንም። እንደኛው ሰዎች መሆናቸውን እናውቃለን። ግና በእኛና በአላህ መካከል አማካይ/አገናኝ/ እና አማላጅ እንዲሆኑልን ነው የምንሻው ይላሉ።.... የጥንት አረብ አጋሪዎችም እንዲሁ ነበር የሚያስቡት” (ገፅ 40 ቅንፍ የመፅሀፉ)

ስለዚህም ለማሻረክ አንድን አካል ጌታና አምላክ ብሎ መጥራት የግድ አይደለም ማለት ነው። ከዚህ ይልቅ ልክ እንደ አረቦቹ አማላጆቻችን ናቸው ብሎ ትምክህትን በእነርሱ ላይ መጣል ራሱ ጣዖት አምልኮ ነው ማለት ነው።

## ነገረ-ምልጃን የተመለከቱ ጥያቄዎች

1) በፍርድ ቀን ለምልጃ ብቁ ከሚያደርጉ መስፈርቶች አንዱ ሐጢያት አልባነት መሆኑን በተለምዶ 'የምልጃ ሐዲስ' በሚል ከሚታወቀው ሐዲስ ተረድተናል። ይህ ከሆነ መሐመድን ጨምሮ ከሁሉም ነቢያቶች በተለየ ሐጢያት የሌለበት ኢየሱስ ነው ለምልጃ ብቁ የሚሆነው? ወይስ ብዙ ጊዜ በአላህ የተገሰፀው መሐመድ? ሐጢያት ያለባቸው እርሳቸውስ እንዴት ነው የሚድኑት? በምህረት ካላችሁኝ እኛስ በምህረት ያለ አማላጅ ሊያድነን የማይችልበት ምክንያት ምንድን ነው?

2) በተለያዩ ሐዲሶች ላይ አላህ የነቢዩ መሐመድን ልመና ሲጥለው እንመለከታለን። ለምሳሌ በአንደኛው ሐዲስ(Muslim2890) መሠረት አላህን ሶስት ነገር ጠየቅኩት። ሕዝቤ በድርቅ፣ በጎርፍና በእርስ በርስ ግጭት እንዳይጠፉ ለመንኩት። የድርቁና የጎርፉን ሲቀበለኝ የእርስ በእርስ ጦርነቱን በተመለከተ የለመንኩትን ልመና ግን ውድቅ አደረገብኝ ብለዋል። በሌላ ቦታ ደግሞ ረዳታቸው አቡጧሊብ በጀሐነም እንዳይገባ አላህን በለመኑት ጊዜ ጥሩ ስላደረገላቸው የእሳቱን ጥልቀት እስከ ቁርጭምጭሚቱ በማድረግ ይቀንስለት ከሆነ እንጂ ጨርሶ ሊምረው እንደማይችል በመግለፅ ልመናቸውን ውድቅ እንዳደረገባቸው እናነባለን። ጥያቄው፡- ከአንዴም ብዙ ጊዜ ልመናቸውን እያጣጠለ ውድቅ ያደረገባቸው ነቢይ፤ በፍርዱ ቀን ከሚገለጠው የአላህ ቁጣ በልመናቸው ያድኑኛል ብሎ ማመን ተላላነት አይሆንም ወይ? የሚል ነው።

3) ነቢዩ መሐመድ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለጅኒዎችም መላካቸው የሚታመን ነው። በተጨማሪም ጅኒዎችም ልክ እንደ ሰው ሁሉ በእምነትና በመልካም ስራቸው ጀነት እንደሚገቡ(ሱራ7:179; 11:119; 32:13-14 ይመ) እንዲሁም በመጨረሻውም ዘመን በምድር ቆይታቸው ለሰሩት በጎም ሆነ ክፉ ስራ እንደሚጠየቁ ይታመናል(ሐሩን ያህያ 'የውመል ቂያማ' ገፅ 66 ይመ)። ይህ እውነት ከሆነ ጥያቄው ምልጃቸው ጅኒዎቹንም ያካትታል ወይስ ለሰዎች ብቻ ነው? ካላካተተ ለምን? የሚያካትት ከሆነ ደግሞ 'ጅኒዎቹንም እንደሚያካትት' ያረጋገጣችሁበትን ማስረጃ ከየት አገኛችሁት?

4) ምልጃን የሚቃወሙ ሙስሊሞች ሳይቀር 'የፍትሐት ፀሎት/Funeral prayer/' እስላማዊ መሠረት ያለው እንደሆነ ያምናሉ፣ ይቀበላሉም። የፍትሐት ፀሎት ደግሞ በፈጣሪ ፊት ከሐጢያቱ የተነሳ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል ተብሎ የሚታመነን ሟች ለማፅደቅ የሚደረግ ፀሎት ነው።( *ሣኒ ሐቢብ 'ስለ እስላም..' ገፅ 75 ይመ*) ጥያቄው፡- የፍትሐት ፀሎትን አፅድቆ፣ ምልጃን የሚኮንን አመክንዮ አለ ወይ? የሚል ነው። ነው ወይስ 'ምልጃ' ከሚለው ስም ጋር ነው ፀባችሁ?

5) በ ቡሐሪ160 መፅ4 ቁ. 26 ላይ የትጥበት/ዑዱ/ ስርአትን ደንቡን ጠብቆ የፈፀመና የግዴታ የጀመዓ ሰላቶችን የሰገደ ሰው እስከሚቀጥለው የሶላት ሰዓት ድረስ የሚሰራቸው ሐጢያቶቹ እንደሚሰረዩ ተገልጿል/…Allah will forgive his sins committed between that prayer and <u>the next prayer</u>/"(*ተመሣሣይ ሐሳብ፡-* በሱናን አቡዳውድ መፅ10 ቁ.1737 ይገኛል። If anyone puts on ihram for Hajj or Umrah from the Aqsa Mosque to the sacred mosque, his former and his later sins will be forgiven, or he will be guaranteed paradise'። ጥያቄው፡- የወደፊት ሐጢያትን ማሰረይ ማለት ምን ማለት ነው? ለሐጢያት ዕውቅና መስጠትስ አይሆንም ወይ?

6) ታላቁ የእስልምና ምሁር ኢማሙ አልገዛሊ በእምነት አንቀፃቸው ቁ.24 ላይ ገሐነም የሚገቡ ሙስሊሞች 'ሁሉም በየተራ በምልጃ አማካኝነት መውጣታቸው የማይቀር ሲሆን ምልጃ የማያገኙ ሰዎች ደግሞ በአላህ ፀጋ/by the grace of Allah/ እንደሚወጡ ገልፀዋል(*<u>Watt pg. 78 ይመ</u>*)። ጥያቄው፡- በአላህ ፀጋ ከጀሐነም የሚወጡት ሙስሊሞች የነቢዩን ወይንም የሌላ ወዳጆቻቸውን ምልጃ ያላገኙበት ምክንያት ምንድን ነው? ደግሞስ ሙስሊሞች ለሰሩት ሐጢያት ለመቀጣት ጀሐነም የሚወርዱ ከሆነ የነቢዩ ምልጃ በጀሐነም ያለን ቆይታ ማሳጠር እንጂ ጨርሶውኑ ጀሐነም ከመግባት አንፃር አይጠቅምም ማለት ነው?

7) አቡሑረይራ የዘገበው ሆኖ በሙስሊም199 መፅ1 ቁ.397 በሚገኝ ሐዲስ ነቢዩ መሐመድ አላህ ለሁሉም ነቢያቶች ለህዝባቸው ይጠይቁበት ዘንድ አንድ የሚመለስ ፀሎት ሰጥቶ ነበር። ነገር ግን ሁሉም ነቢያቶች ለህዝባቸው

የተሰጣቸውን የምልጃ ሲጠቀሙ እኔ ብቻ በፍርዱ ቀን ህዝቤን ላድንበት ፀሎቱን ቆጠብኩት ብለዋል"

ጥያቄው፡- ፀሎትን መቆጠብ ምን ማለት ነው? ለምንስ አስፈለገ? ነቢያቶች ለሕዝባቸው ይፀልዩበት ዘንድ የተሰጣቸውን ምልጃ መፈፀማቸውን የሚያስረዳ ከእስላማዊ ምንጮች ውጪ ማስረጃ ይገኛል? (ይህ ትረካ ከሌሎቹ ነቢያቶች በተቃራኒ፣ ነቢዩ የሕዝባቸው የድነት ጉዳይ ግድ እንደሚላቸው አድርገው በማቅረብ ሌሎቹን ነቢያቶች ግዴየለሾች ለማድረግ አስበው የተረኩት ይመስላል)

8) ጀሐነም የገቡ ሙስሊሞች እንደ ስራቸው መጠን ተራ በተራ ከጀሐነም እንደሚወጡ ያለው አስተምህሮ በምልጃ አማካኝነት እንደሚወጡ ካለው አስተምህሮ ጋር እንዴት ይገናዘባል?

9) በቡሐሪ ቅፅ4 መፅ55 ቁ.544 መሠረት ጀነት የሚገቡ ሰዎች መልካቸውም ቁመታቸውም(30ሜትር) የአዳምን እንዲመስል እንደሚደረግ ተገልፆል(በሌላ ሐዲስ የሁሉም የጀነት ሰዎች ዕድሜ 30 ወይንም 33 እንደሚሆን ተገልፆል)። ጥያቄው፡- ሁሉንም የጀነት ሰዎች መልካቸውን ጨምሮ አንድ አይነት የማድረጉ ምክንያት/ፋይዳ/ ምንድን ነው?

10) ፍትሐት ሐጢያት ይኖርበታል ተብሎ ለሚታመን የሚታመን አካል በአላህ ፊት ሞገስ ያገኝ ዘንድ/ምህረት እንዲሰጠው/ ለማድረግ የሚቀርብ የፀሎት አይነት ከሆነ። ለነቢዩ መሐመድ የፍትሐት ፀሎት ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?(Sunan Ibn Majah 1628 https://islamqa.org/?p=7774)

11) መረጃዎች መሠረት ክፉ ስራቸው እኩል ሆኖባቸው ጀነትም ጀሐነምም መግባት ሳይችሉ በመካከለኛ ስፍራ እንዲሰፍሩ የሚደረጉ ነፍሳትን(Wahid 'Creed...' pg. 181)፣ እንዲሁም ከጀሐነም የሚያወጣቸው አማላጅ ያላገኙ/የሌላቸው/ ሰዎችን(*Watt '... Creed' pg. 78)* አላህ ያለ አማላጅ በፀጋው/grace/ ብቻ ምህረት አድርጎላቸው ጀነት እንደሚከታቸው ይታመናል። ይህ ማለት አላህ ሰዎችን ጀነት እንዲገቡ ከፈለገ ያለ አማላጅ ሊያስገባቸው ይችላል ማለት ነው። ይህ ከሆነ የምልጃ አስፈላጊነት ምንድን ነው? ስለምንስ አላህ ሁሉን ሰው እንደ ጥፋቱ የሚገባውን ያህል ከቀጣው በኋላ ወደ ጀነት አይከተውም?

12) ሐዲሶች መሠረት የነቢዩ መሐመድ ምልጃ በዋናነት ከባድ ወንጀል/Major Sin/ ለፈፀሙ እንደሚውል ይታወቃል። በቡሐሪ ቅፅ2 መፅ24 ቁ.485 መሠረት ከሆነ ግን ሐጢያትን/ግፍን/ በእንስሳ ላይ እንኳን የፈፀሙ ሰዎች የነቢዩ መሐመድ ምልጃ እንደማይደርሳቸው እንረዳለን። ጥያቄው ይህ ምን ማለት ነው የሚል ነው። ምልጃቸው ለሐጢያተኞች/በዚህ ዐውድ በእንስሳ ላይ ግፍ ለፈፀሙ/ ካልሆነ ለማን ሊሆን ነው? ሐጢያትን ላልፈፀሙ ፃድቃን እንደማትሉኝ ተስፋ አለኝ።

13) በቡሐሪ ቅፅ1 መፅ11 ቁ.588 እና በሌሎችም ሐዲሶች መሠረት ነቢዩ መሐመድ የምልጃ መብት(አላህ የእናንተ የምማልድበትን ፈቃድ) እንዲሰጠኝ ማልዱልኝ ማለታቸው ይታወቃል። ይህ ብቻ አይደለም በዚሁ በተጠቀሰውና በሌሎችም ሐዲሶች መሠረት በጀነት ከፍተኛውን የክብር ስፍራ(Superior place -- ሌሎች ሐዲሶች ስፍራው አል-ዋሲላህ እንደሚባል ፅፈዋል) እንዲያጎናፅፈኝ ማልዱልኝ ማለታቸው ይታወቃል። ጥያቄው፡- አማላጁ ራሱ ሌላ አማላጅ ካስፈለገው(*ይረዳናል ያልነው የእኛን እርዳታ ከጠየቀ እንደማለት ነው*) እንዴት ልባችንን ልንጥልበት እንችላለን? ደግሞስ አማላጅ እንዲያደርጋቸው በማለት ለእርሳቸው የምናቀርበው ልመና የሚሰማ ከሆነ በቀጥታ እርሱ ራሱ ምህረት እንዲያደርግልን ለምን አንጠይቀውም? ባንማልድላቸውስ የምልጃውን ፈቃድ አያገኙም ማለት ነው? ደግሞስ በጀነት የሚገኝ የክብር ስፍራ ምድር ላይ በሰራነው መልካም ስራ መጠን ነው የሚገኘው ወይስ በፀሎት(ሊያውም በሌሎች ሰዎች ፀሎት)? ነቢዩ መሐመድ ሰዎች ባይፀልዩስ ምድር ላይ የሰሩት 'መልካም ስራ' ብቻ ስፍራውን ለማግኘት ብቁ ስለማያደርጋቸው ነው የፀሎት ድጋፍ ያስፈለጋቸው?

14) የነቢዩ መሐመድን ምልጃ በተመለከተ እስላማዊ ምንጮች ምልጃው ማንን እንደሚመለከት ባለ ነጥብ ላይ ልዩነት አሳይተዋል። ምልጃቸው ታላቅ ሐጢያት/Major sin/ ለፈፀሙ ነው የሚሉ እንዳሉ ሁሉ ምልጃቸው ለሁሉም ሙስሊሞች ነው የሚሉ እንዲሁም ምልጃቸው ለሰው ልጅ ሁሉ(ሙስሊም ላልሆነውም) ነው የሚሉ መረጃዎች ሞልተዋል። ጥያቄው፡- ትክክለኛው የቱ ነው? በብዛት ያሉት መረጃዎች ታላላቅ ሐጢያት ለሰሩ ነው የሚል እንደመሆኑ ምልጃቸው ታላላቅ ሐጢያት ለሰሩ ነው ብላችሁ ከመለሳችሁ አያይዤ የምጠይቀው ጥያቄ ለሁሉም

ሙስሊሞች ወይንም ለሰው ልጅ በሙሉ ነው የሚሉትን መረጃዎች የማትቀበሉበት ምክንያት ምንድን ነው? በሚል ነው።

15) በ አልቡሐሪ6055 መፅ78 ቁ.85 ባለ አንድ ታሪክ መሠረት ነቢዩ መሐመድ በመቃብር እያለፉ ሳለ በሰሙት ስቃይ የተነሳ ተቀጪዎቹ ሰዎች ስቃያቸው ይቀንስላቸው ዘንድ የዘንባባ ዝንጣፊ በመውሰድ እና በመቃብሮቹም ላይ በማድረግ 'ቅጠሎቹ እስከሚደርቁ ድረስ ቅጣታቸውን ቢያቀልላቸው ብዬ ነው' ማለታቸው ይታወቃል። ጥያቄው ልመናቸው/ሙከራቸው/ እንደሚሳካ ስለምን እርግጠኛ አልሆኑም? ደግሞስ ለተወሰኑ ቀናት ብቻ ከስቃይ የሚያሳርፍ ልመና ከሚያቀርቡ ይልቅ፣ ለዘላለም ከስቃያቸው የሚገላግላቸውን(ልመናቸው ተሰምቶ ስቃዩ ቢቀንስ እንኳን ቅጠሎቹ ሲደርቁ ተመልሶ እንደሚጨምር ልብ ይሏል?) ልመና ስለምን አላቀረቡላቸው?(ልመናቸው ይመለሳል፣ አይመለስም የሚለውን አቆይተን)፣ ደግሞስ ስቃያቸው እንዲቀንስ ከመጠየቅ ይልቅ ስለምን እንዲቆም አልጠየቁላቸውም?(ስቃያቸው ቢቀንስ አሉ እንጂ ስቃያቸው ቢቆም እንዳላሉ ልብ ይሏል?)

16) ታዋቂ በሆነው የምልጃ ሐዲስ መሠረት ነቢዩ መሐመድ በገሐነም እየተሰቃዩ ያሉ ሙስሊሞችን ተራ በተራ እንደየስራቸው መጠን(የባቄላን ያህል መልካም ነገር ያለው ይቀድማል፣ ቀጥሎ የስንዴን ያህል መልካም ነገር ያለው ይከተላል በስተመጨረሻ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል መልካም ነገር ያለው ይወጣል) እንደሚያውጧቸው ይታመናል። ጥያቄው እንበልና የስንዴ ቅንጣት ያህል መልካም ነገር ያለው ሙስሊም ለሐጢያቱ በቂ ነው የሚባል ቅጣት ተቀጥቶ ቢጨርስ ነገር ግን ነቢዩ መሐመድ ባያማልዱት ከጀሐነም ይወጣል ወይስ ይቆያል?

17) እንደሚታወቀው ምልጃ ከፍርድ ቀን በኻላ የሚፈፀም ነው(Nerina pg. 69)። ግና ከዚያ በፊት ሐጢያተኛ ሙስሊሞች ለሐጢያታቸው በመቃብር ቅጣት እንደሚቀጡ ይታመናል። የቅጣቱ አላማም ሐጢያታቸውን ለማንፃት እንደሆነ ይታመናል። ይህ ከሆነ ለሐጢያታቸው ስርየት የሚሆን ቅጣት ከተቀበሉና ከነፁ በኻላ ምልጃ ያስፈለገበት ምክንያት ምን ይሆን? ነው ወይስ ቅጣቱ ሐጢያታቸውን በደንብ ስለማያጥበው ነው? ደግሞስ የነቢዩ ምልጃ ከመቃብር ቅጣት ለማዳን ለምን አያገለግልም?

18) ነቢዩ መሐመድ ለሌሎች ነቢያቶች ያልተሰጡ 5ት ነገሮች ተሰጥተውኛል ባሉበት ሐዲስ(ቡሐሪ1:199-200; 331 ይመ)፣ ተሰጠኝ ካሉት አንደኛው ምልጃ እንደሆነ ገልፀዋል። ይሁንና ሌሎች ነቢያቶች እንደሚያማልዱ የሚታወቅ ከሆነ 'ምልጃን ለሌሎች ነቢያቶች አልተሰጠም'ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ምናልባት ከሌሎች ነቢያቶች የተለየ ባሕርይ/መገለጫ/ አለው ለማለት ፈልገውም ከሆነ የእርሳቸው ምልጃ በምን እንደሚለይና ለምን እንደተለየ ብትገልጡልን?

19) ታዋቂ የሆነው የምልጃ ሐዲስ የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚያስነሳ ነው፡- አማልዱን እያሉ በዙር የሚጠይቁት ሙስሊሞች መሆናቸው ይታወቃል(ምክንያቱም በስተመጨረሻ ነቢዩ መሐመድ ጥያቄያቸውን ተቀብለው ማልደዋልና። በእስልምና ደግሞ ነቢዩ የሚማልዱት ለሙስሊሞች ብቻ እንደሆነ ስለሚታወቅ ጠያቂዎቹ ሙስሊሞች እንደሆኑ እንረዳለን)። ይህ እውነት ከሆነ 'ምልጃቸው መሬት ጠብ የማይልላቸው/የሚሰምርላቸው/ ነቢይ - ነቢዩ መሐመድ ብቻ ናቸው!' ብለው የሚያምኑ ሙስሊሞች በቀጥታ መሐመድን መጠየቅ ሲገባቸው ከአዳም ጀምሮ የሚጠይቁበት ምክንያት ምንድን ነው?(ሊያውም አስጨናቂ ከመሆኑ የተነሳ ፋታ በማይሰጠው በዛን ጊዜ) እንዲያማልዱ በሚጠየቁ ጊዜ ሐጢያቶቻቸውን እያሰቡ ብቁ እንዳልሆኑና፣ ጭራሽ ለራሳቸውም ጭምር እንደሚፈሩ መናገራቸው እስከዚያች ዕለት ድረስ ሐጢያታቸው ስላልተሰረየ ነውን? ከሆነ(ካልተሰረየ) የነቢዩ መሐመድን ሐጢያት ይቅር ብሎ የእነርሱን ይቅር ያላለበት ምክንያት ምንድን ነው? ካልተሰረየ በመቃብር ቅጣትስ ተቀጥተዋል ማለት ነው? ካልተሰረየስ እንዴት ገነት ገቡ(ነቢዩ መሐመድ በሚራጅ ጉዞ ወቅት ነቢያቶችን በጀነት እንዳዩአቸው መናገራቸውን ልብ ይሏል)? ምልጃውን በዘገቡት በሁሉም ሐዲሶች ነቢያቶቹ ሐጢያታቸውን እያሰቡ 'እኔ ለማማለድ ብቁ አይደለሁም' እንዳሉ ሁሉ ኢየሱስም 'ለማማለድ ብቁ አይደለሁም' ብሏል። ሐጢያት ከሌለበት ብቁ የማይሆንበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል? ምድር ላይ ሰዎች 'የአምላክ ልጅ ነው!' ብለው ስላመለኩት ካላችሁ፣ 'አምልኩኝ' ባላበት ተጨባጭ ምድር ላይ ሰዎች ማምለካቸው በእርሱ ላይ ሐጢያት የሚሆንበት አግባቦ ምንድን ነው?

20) በሳሂህ አልቡሐሪ3342 መፅ60 ቁ.17 እና በሳሂህ አል-ቡሐሪ349 መፅ8 ቁ.1 መሠረት ነቢዩ መሐመድ ዑማቸው 50 ሶላት ሲደፈደፍበት እንዴት ተስማሙ? ምናልባት ስለ ዑማቸው ዐቅም በቂ እውቀት ስላልነበራቸው ነው ከተባለ እንዴት ታዲያ ከእርሳቸው በመልከዐምድር በጊዜም ሩቅ የሆነው ነቢዩ ሙሳ ከእርሳቸው በተሻለ ሊያውቅ ቻለ(ሙሳ ስለ መሐመድ ዑማ ስላላቸው ዐቅም እንደማያውቅ ይህንኑ ታሪክ በያዙ ሌሎች ሐዲሶች ላይ/Versions/

5ት ከታዘዘ በኂላ ራሱ አይችሉም አስቀንስ ማለቱ ይጠቁማል)? ደግሞስ አላህ '5ቱ ሰላት እንደ 50ው ሶላት ምንዳ ነው ትዕዛዜ አትለወጥም' በማለት ከ5ት ሶላት አልቀንስም እያለ ሙሳ ሂድና አስቀንስ ያለው ከአላህ በላይ ስለ ሙሐመድ ዑማ ስለሚያውቅ/ስለ ራራ/ ነው? ወይስ የአላህን ድንጋጌ ስለናቀ ነው? ጥያቄ ወይንም ቅሬታ ካለበትስ ስለምን ራሱ ሙሳ በቀጥታ አሏህን ከመጠየቅ ይልቅ በመሐመድ በኩል መጠየቅን መረጠ? ለዚህ የሚኖረው ምላሽ ስለ መሐመድ ዑማ በቀጥታ የሚመለከተው ሙሐመድን ስለሆነ ነው የሚል ከሆነ አስከትለን የምናነሳው ጥያቄ ታዲያ ስለ ነፍሳችንስ ድነት ከእኛ በላይ መሐመድ አግብቶት ነው ወይ ያማልደናል ብለን የምንታመንበት? 5ቱ ሶላት እንደ 50ው ያለ ምንዳ ያላቸው ከሆነ መጀመሪያውኑ አላህ ስለምን 5ት ሶላት አላዘዘም? ደግሞስ መጀመሪያ ከነበረው 50 ሶላት 5ት እስኪደርስ ድረስ ሲለዋውጥ ቆይቶ 5ት ላይ 'ደንግጌያለሁ ትዕዛዜ አይለወጥም' ማለቱ ትርጉም ይሰጣል ወይ

# <u>ማጠቃለያ፡- የንስሀ ጥሪ</u>

በምልጃ ዙሪያ የነበረን ውይይት እንግዲህ ይህን ከላይ የቀረበውን ይመስላል። ሙስሊሞች ሲነገራቸውና ሲመስላቸው ከነበረው እውነት በተቃራኒ ነቢዩ መሐመድ ሐጢያተኛ መሆናቸውን፣ በዚህም የተነሳ ለምልጃ ብቁ አለመሆናቸውን፣ የነቢዩን አማላጅነት የሚናገሩ ሐዲሶች እርስ እርስ ከመጣረሳቸው በላይ ከባባድ የሆኑ ስነመለኮታዊና ስነምግባራዊ ጥያቄን የሚያስነሱ መሆኑን፣ በነቢዩ መሐመድ ምልጃ ላይ እንድንተማመን የሚያስችል አንዳችም ሰነዳዊና አመክንዮአዊ መሠረት የሌለ መሆኑን እንዲሁም ምልጃቸው ለማን፣ በምን፣ እንዴት እንደሚፈፀም ግልፅ የሆነ መረጃ አለመኖሩን አይተናል።

በመሆኑም በውይይታችን ያነሳናቸው እያንዳንዱ ሙግቶችና ማስረጃዎች የነቢዩ መሐመድን አማላጅነት ተስፋ እንድናደርግ ከማድረግ ይልቅ አስተምህሮው እንዴት ባለ ደካማ መረጃና ምክንዮ እንደተገነባ የሚያሳዩ በመሆናቸው ልንተማመንባቸው እንደማይገባ አሳይተዋል ብለን እናምናለን።

ይህ ከሆነ ዘንዳ፡- ይህን ፅሁፍ ለሚያነቡ ሙስሊም ወገኖቻችን ይህን ምክር ሳንለግስ መቋጨት የሚኖርብን አይመስለኝም።

ውድ ሙስሊም ወገኖች፡- እስልምና ከምታምኑትም ሆነ ሲነገራችሁ ከቆያችሁት በተቃራኒ ለአኺራ ሕይወታችሁ አንዳችም ተስፋ የሌለው እምነት ነው። ለዚህም እንኳንና በብዙ የሐጢያት ልምምድና ድካም ውስጥ የምትመላለሱት እናንተ ቀርቶ ከሰው ልጆች ሁሉ ይልቅ ለአላህ የተገዙ ናቸው ብላችሁ የምታምኗቸው ነቢዩ መሐመድና ተከታዮቻቸውም ጭምር ስለ ዘላለም ሕይወታቸው ሲያስቡ በጭንቀትና በታላቅ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይመላለሱ እንደነበር የሚያሳዩት ግለ ታሪኮቻቸው ምስክር መሆን ይችላሉ።

ምናልባት ነቢዩ ይቆሙልኛል፣ ይሟገቱልኛል ብላችሁ ተስፋ አድርጋችሁ ሊሆን ይችላል። ከላይ የነበረን ውይይት እንኳን ለእናንተ ጠበቃ ሊሆኑ ቀርቶ ለራሳቸውም ያልበቁ ነቢይ መሆናቸውን አሳይቷችኋል ብዬ አምናለሁ።

ወይም ደግሞ በአላህ ምህረትም ተማምናችሁ ከሆነ አስረግጬ የምነግራችሁ ከእናንተ ይልቅ ነቢዩ መሐመድና ሶሐቦቻቸው የአላህን ምሕረት የማግኘት ዕድሉ ያላቸው መሆኑን ነው(ምሕረት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ከእናንተ ይልቅ ነቢዩ መሐመድና ሶሐቦቻቸው ማሟላት ይችላሉ ለማለት ነው)። ይሁንና ግን የጀሐነምን እሳት ባሰቡ ቁጥር '...ምናለ ሰው ሆኜ ባልፈጠር?' እስኪሉ ድረስ ጭንቀት ይገባቸው እንደነበር የሚያትቱ ታሪኮቻቸውን አንብባችሁሃል።

ልላችሁ የፈለግኩት ምንድን ነው? የአሏህን ምህረት አገኛለሁ ብላችሁ ተስፋ አታደርጉ እያልኩ ነው። የአላህ ምህረት እንኳን ለእናንተ ቀርቶ 'ሕይወታቸው የቁርአን ነፀብራቅ ነው!' ለሚባልላቸው ነቢይ እንኳን አልደረሰምና።

ባይሆን ይህን የምጠቁማችሁን የመፍትሄ ሀሳብ ልብ ብላችሁ ስሙኝ፡- በወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ልክ እንደ እናንተ የሕይወት ጥያቄ ላለባቸው ሰዎች ከሰጠው ምክር አንዱ እንዲህ የሚለው ነው "…. እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ <u>*ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ*</u>። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ <u>*ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ*</u>" --ማቴ 11:28-29

ውድ ሙስሊሞች፡- የምትፈልጉት ምንድን ነው? ነፍሳችሁን ለአንዴና ለመጨረሻ ከጭንቀት የሚገላግል ዕረፍት ከሆነ። እንግዲያውስ ከላይ ባነበብነው ጥቅስ መሠረት ኢየሱስ 'ወደ <u>እኔ ኑ እኔም አሳሬፋችሃለሁ</u>……<u>ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ</u>' ሲል ተስፋ ሰጥቷችሃልና ወደ ኢየሱስ ኑ!

አዎን እረፍት ከፈለጋችሁ . . .  ወደ ኢየሱስ ኑ!

## ሕዳግ መዘክር

በዚህ ፅሁፍ ላቀረብኳቸው መረጃዎች ምንጮችን የጠቀስኩበት መንገድ ያልተለመደ ሊሆን ይችላል። ከመፅሀፉ ርዕስ አንደኛውን ቃል ብቻ በመውሰድ ወይንም ከፀሐፊው/ከፀሐፊያኑ የአንዳቸውን ስም በዘፈቀደ በመውሰድና መረጃው የተገኘበትን ገፅ በማስከተል ጠቅሻለሁ። ግልፅ ለማድረግም ከዚህ በታች የትኛው አጠቃቀስ የትኛውን መፅሀፍ እንደሚወክል ደምቆ በተፃፈው(Bold statement) ሐረግ አመልክቻለሁ።


- ሼሕ ሰይድ መሐመድ ሳዲቅ 'እስልምናና ሚስዮናዊያን' 1962ዓም ተዘጋጀ መስከረም 2016 ታተመ አሳታሚ ሉባባ ሰይድ መሐመድ ሳዲቅ። ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው ሰይድ 'ሚሲዮናዊያን...' ገፅ. ተብሎ ነው።***
- ሐጅ መሐመድ ሣኒ ሐቢብ 'ስለ እስላም ለማወቅ፡ በአማርኛ ቋንቋ' አሣታሚና አዘጋጅ ሐጅ መሐመድ ሣኒ ሐቢብ ። ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው ሣኒ ሐቢብ 'ስል እስላም....' ገፅ. ተብሎ ነው።***
- ፐ/ር ኢማም ዩሱፍ አልቀረዳዊ 'ተውሒድ ይዘቱና ሚናው' ትርጉም ኡስታዝ ሐሰን ታጁ፣ አሳታሚ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፣ ዓመተምህረት አልተጠቀሰም። ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው አሊቃርዳዊ ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Jane Idleman Smith Yvonne Yazbeck Haddad 'The Islamic Understanding of Death and Resurrection', 1981, STATE UNIVERSITY OF NEW YORK PRESS,ALBANY ። ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Haddad ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Juan E. Campo 'Encyclopedia of Islam', 2009, Printed in the United States of America. ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Campo ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Ibn Hajar Al-Asqalani 'Selections from the fath al-Bari' 2000, Translated by Abdal Hakim Murad, Muslim Academic Trust. ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Hajar ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Annemarie Schimmel 'And Muhammed is his messenger፡ The veneration of the prophet in Islamic Piety' 1985, University of North Carolina Press. ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Annemarie ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Alpha Mahmoud Bah(D.r) 'Glimpses of life after death', 2003, revised edition, Writers Club Press, New York, ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Bah ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Shiekh Abdulaziz bin Abdullah bin baz 'The Authentic Creed: and the invalidators of Islam', 2001, Printed by the the ministry of Islamic affairs. ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Invalidator ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Nerina Rustomi 'The Garden and The Fire: heaven and hell in Islamic culture' 2009,Columbia University Press ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Nerina ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Muhammed Mustafa Al-Jibaly 'Life in Al-Barzakh: from Death untill resurection' 2006, 2nd edition, Publisher Al-Kitaab and As-Sunnah ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Barzakh ገፅ. ተብሎ ነው።***
- ሀሩን ያሕያ 'የውመል ቂያማ' ትርጉም አሕመድ ሁሴን(አቡ ቢላል) አሳታሚ ነጃሺ ማተሚያ ቤት ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው ያሕያ ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Asiyah Banu 'An Inquiry into intercession', 2012 Translated by Mahboobeh Morshedian, source URL https://www.al-islam.org/message-thaqalayn/vol-13-no-2-summer-2012/inquiry-intercession-shafaah-asiyah-banu#comment-0 ***ይህ ምንጭ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Asiya ገፅ. ተብሎ ነው።***

- Dr. Muhammed Muhsin Khan ‘Translation of the meanings of Sahih Al-Bukhari’ vol .1, 1997, published by Darussalem, Kingdom of Saudi Arabia ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Muhsin ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Mahmoud Ayoub ‘A Muslim view of Christianity: essays on dialogue', 2007, Orbis publisher, New York. ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Ayoub ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Ibn Qayyim al-Jawziyyah ‘Driving the souls to the abodes of happiness' Translated by Abdul Ali Hamid ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Driving ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Dr. Mufti Abdul Wahid, 'CREED OF ISLAM', Augest 2010, Head of Fatwa and Research Center, lahore, ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Wahid ገፅ. ተብሎ ነው።***
- ሳሂህ አብዱል ‘መቃብር መካነ-ፍዳ’ ጥር 2017 ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው ሳሂህ አብዱል ገፅ. ተብሎ ነው።*** ሊንኩም የሚከተለው ነው https://t.me/realsahih/927)።
- Ibn Taymiyyah ‘Expounds on Islam' compiled and Translated by Muhammed Abdul-Haqq Ansari, 2000G.C ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Expounds ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Norman L. Geisler and Abdul Saleeb ‘Answering Islam: The Cresent in the light of the cross' May 2003, 2nd edit, printed in USA. ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Geisler ገፅ. ተብሎ ነው።***
- Christian Lange ‘Locating Hell in Islamic Tradtions, 2016 BRILL ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው Lange ገፅ. ተብሎ ነው***
- ኢማም አልገዛሊ ‘ኢሕያዕ ዑሉሙዲን’ ትርጉም መሐመድ ሰዒድ ነጃሺ ማተሚያ ቤት ***ይህ መፅሀፍ በዚህ ፅሁፍ የተጠቀሰው ኢሕያዕ ገፅ. ተብሎ ነው***